www.abyssinialaw.com

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
ዝክረ ሕግ

ZIKRE-HIG
OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

8ኛ ዓመት ቁጥር 3
8th Year No.3

ባህር ዳር ሰኔ 18 ቀን/1995 ዓ/ም
Bahir Dar 25th Day of June 2003

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL
OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 79/1995 ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልል የቤተሰብ ሕግ
ማጽደቂያ አዋጅ

## CONTENTS

PROCLAMATION NO. 79/2003 – THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
FAMILY CODE APPROVAL PROCLAMATION.

www.abyssinialaw.com

## የግድፈት ማረሚያ /CORRIGENDA/

ገጽ 32 አንቀጽ 94 /4/ « ፍችውን አስቀድሞ በመወሰን » የሚለው « ፍችውን አስቀድሞ በመወሰን. » ተብሎ ይነበብ፡፡

ገጽ 37 አንቀጽ 110 /3/ « ... በተደጋጋመ ... » የሚለው « በተደጋገመ » ተብሎ ይነበብ፡፡

ገጽ 42 አንቀጽ 124 /3/ « ... ውሳኔ እንዲሰጥ ... » የሚለው « ... ውሳኔ እንዲሰጥ ... » ተብሎ ይነበብ፡፡

ገጽ 48 አንቀጽ 144 « አንድ ሰው በክብር መዝገብ ሹም ፊት ቀርቦ አባት መሆኑን በመገለጽ..» ተብሎ ይነበብ

ገጽ 55 አንቀጽ 162 /2/ « በፍርድ» የሚለው ቃል ተሰርዞ ይነበብ፡፡

ገጽ 58 አንቀጽ 172 /3/ « ልጁ ሃያ አመት ሳይሞላው የሞተ እንደሆነ እርሱ ከሞተ በኋላ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ወራሾቹ ክስ ለማቅረብ አይችሉም» ተብሎ ይነበብ፡፡

ገጽ 83 አንቀጽ 241 « ... በሌላ ማናቸውም ምክንያት... » ተብሎ ይነበብ፡፡

ገጽ 86 አነቀጽ 249 /1/ « ... ተግባር ማከናወኑ በራሱ ላይ ከበድ ያለ ... ይችላል፡፡ » ተብሎ ይነበብ፡፡

ገጽ 138 አንቀጽ 56 /1/ « ... Shall be deposited in the justice body authorized to witness The conclusion of contracts or ... » ተብሎ ይነበብ፡፡

ገጽ 161 አንቀጽ 145 /2/ « Approved by the justice body authorized to witness the Conclusion of contracts.» ተብሎ ይነበብ፡፡

ገጽ 162 አንቀጽ 149 የእንግሊዝኛ ትርጉሙ ተሰርዞ እንደሚተለው ይነበብ፡፡

" The acknowledgement of paternity shall be deemed to be accepted where the persons mentioned in Articles 147 and 148 have not raised any protest against such acknowledgement with in one month after they came know of it".

ገጽ 166 አንቀጽ 161 /1/ " ... approved by the justice body authorized to witness the conclusion of contracts." ተብሎ ይነበብ፡፡

ገጽ 176 አንቀጽ 205 /4/ የተዘለለ በመሆኑ የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ 4 ሆኖ ይነበብ፡፡

"The court shall take special care in investigating the conditions provided in sub-Article /3/ /e/ of this Article, where the adopter is foreigner."

www.abyssinialaw.com

8ኛ ዓመት ቁጥር 3

ባህር ዳር ሰኔ 18 ቀን 1995 ዓ.ም

**አዋጅ ቁጥር 79/1995 ዓ.ም**
**የአማራ ብሔራዊ ክልል የቤተሰብ ሕግ ማፅደቂያ**
**አዋጅ**

**አዋጅ ቁጥር 79/1995 ዓ.ም**
**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ሕግን**
**ለማፅደቅ**
**የወጣ አዋጅ**

የቤተሰብ የህብረተሰብ ተፈጥሮአዊ መነሻ በመሆኑና በህብረተሰብና በመንግስት ያላሰለሰ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን በማመን፣

የመንግሥት ጥበቃ የሚገለጽበት አንዱ መንገድም የቤተሰብ ግንኙነቶችን በሕግ መደንገግና መግዛት መሆኑን በመገንዘብ፤

እስካሁን ድረስ በሀገራችንም ሆነ በክልላችን ፀንቶ የሚሠራበትና የ1952ቱ የፍተሐብሄር ሕግ ክፍልና አካል የሆነው የቤተሰብ ሕግ አሁን ካለንበት እድገት ደረጃና በዋነኛነት ከፌደራሉም ሆነ ከክልሉ ሕግጋተ መንግሥታት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ በማስፈለጉና በተለይም ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ መመሥረት ያለበት መሆኑንና በጋብቻ አፈፃፀም፣በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ የተጋቢዎችን የእኩልነት መብት የሚያስጠብቅ ዝርዝር ሕግ ማውጣትና በሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

የልጆችን ደህንነት፣አስተዳደግና አጠባበቅ አስመልክቶ የክልሉ ሕገ-መንግስትና አገራችን ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች በሚጠይቁት መሠረት ለህፃናት ደህንነት ቀደምትነትን በሚሰጥ መልኩ በሥራ ላይ ያለውን ሕግ አሻሽሎና ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተስማሚነቱን አረጋግጦ መቅረጽ በማስፈለጉ፤

በቤተሰብ ውስጥ የሚነሱ ክርክሮች ፍትሀዊ በሆነና በተቀላጠፈ ሁኔታ ብቃት ባለው አካል እንዲዳኙ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህን እውን ለማድረግም በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ ተፈጻሚነት የሚኖረው የቤተሰብ ሕግ በክልሉ ምክር ቤት ተመክሮበት መውጣት ያለበት በመሆኑ፣

በብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ከዚህ የሚከተለውን አውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልል የቤተሰብ ህግ ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር 79/1995 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ መሰረት ፀድቆ በወጣው የቤተሰብ ህግ ውስጥ፡-

   1. "ክልል" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል ነው፡፡
   2. "መንግስት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፡፡
   3. "አቃቤ ህግ" ማለት የየደረጃው የአማራ ብሔራዊ ክልል አቃቤ ህግ ነው፡፡
   4. "የጋብቻ አስፈፃሚ ባለሥልጣን" ማለት የክብር መዝገብ ሹም ፣የሃይማኖትና የባህላዊ ጉዳዩች ባለሥልጣናት ናቸው፡፡
   5. "ቤተ ዘመድ" ማለት በቅድመ ጋብቻ ትጭጭትም ሆነ በጋብቻ አፈፃፀም ወቅት ታዛቢዎች ወይም እማኞች በመሆን የሚሣተፉ ሠዎችን የሚገልጽ ነው፡፡

3. **ሕጉ ስለሚፀናበት ጊዜ**

   በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣው ሕግ ከማጽደቂያ አዋጁ ጋር በክልሉ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባህር ዳር**
**ሰኔ 18 ቀን 1995 ዓ/ም**
**ዮሴፍ ረታ**
**የአማራ ብሔራዊ ክልል**
**ኘሬዚዳንት**

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ አንድ
## ቅድመ ጋብቻ ትጭጭት

**አንቀጽ 1 መሠረቱ**

1. ትጭጭት ለአካለ መጠን የደረሱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለወደፊት ትዳር እንደሚመሠርቱ በይፋ ገልፀውና የጋብቻ መፈፀሚያ ቀን ቆርጠው በመስማማት የእጮኛውና የእጮኛይቱ ቤተዘመዶች ተወካዮችና ምስክሮቻቸው በታዛቢነት በተገኙበት ሥነ-ሥርዓት ፈቅደው የሚለዋወጡት የርስ በርስ ቃል ኪዳን ነው፡፡
2. የመተጫጨት ውል በቃል ኪዳን ፀንተው በመቆየት ለመፃኢ ትዳር እንዲዘጋጁ ከማድረግ አልፎ እጩ ተጋቢዎቹን ለወደፊት እንዲጋቡ የማስገደድ ውጤት አይኖረውም፡፡
3. በሁለት ሰዎች መካከል ለመጋባት የተደረገ የተስፋ ቃል ልውውጥ ብቻውን በዚህ አንቀጽ መሰረት የትጭጭት ውጤት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 2 የቤተዘመድ ተወካዮችን ስለመምረጥ**

1. ቀዳሚ የትጭጭት ውል እማኞች የሚሆኑት የእጩ ተጋቢዎች ወላጆች ወይም ህጋዊ አሳዳጊዎች ናቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ በተደነገገው መሠረት መፈፀም ያልተቻለ እንደሆነ እጩ ተጋቢዎች በትጭጭቱ ሥነ-ሥረዓት ላይ የሚገኙላቸውን የቤተ ዘመድ ተወካዮች በየራሳቸው ምርጫ ይሰይማሉ፡፡

**አንቀጽ 3 የእጩ ተጋቢዎች ፈቃድ**

እጩ ተጋቢዎች ፈቃዳቸውን ያልሰጡበት ማናቸውም የመተጫጨት ውል በሕግ ፊት አይፀናም፡፡

**አንቀጽ 4 ጋብቻን የሚከለክል ሁኔታ ስለመኖሩ**

በእጮኛውና በእጮኛይቱ መካከል ጋብቻ እንዳይፈፀም የሚከለክል ሁኔታ መኖሩ አስቀድሞ እየታወቀ የሚደረግ ማናቸውም የመተጫጨት ውል በሕግ ረገድ ውጤት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 5 ውሉ ስለሚፈፀምበት ፎርም**

የመተጫጨት ውል በጽሁፍ የሚደረግ ሆኖ እጩ ተጋቢዎችና አራት የቤተዘድ እማኞቻቸው /ሁለት ከወንድ ወገን ሁለት ከሴት ወገን/ ሊፈርሙበት ይገባል፡፡

**አንቀጽ 6 ትጭጭቱ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ**

የመተጫጨት ውሉ በተደረገበት ወቅት የጋብቻ መፈፀሚያ ቀን ሣይቆረጥ ቀርቶ እንደሆነ እጩ ተጋቢዎች የጋብቻቸውን ሥነ-ሥርዓት የሚፈፅሙበት ውሉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 7 ስለ ውሉ መጣስ ወይም አለመፈ ፀም**

ከእጩ ተጋቢዎች አንዱ ከዚህ በላይ በተፃፈው አንቀጽ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ በቂና ሕጋዊ ምክንያት ሣይኖረው የታሰበውን ጋብቻ አልፈጽምም ሲል እምቢ ያለ እንደሆነ ወይም ልዩ ልዩ መሰናክሎችን በመፍጠር ጋብቻው በወቅቱ እንዳይፈፀም ሆነ ብሎ ያዘገየ እንደሆነ የመተጫጨት ውሉ በዚሁ ወገን እንደተጣሰ ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 8 የውሉ መጣስ ስለሚያስከትለው ውጤት**

1. የመተጫጨት ውሉን ያፈረሰ ማናቸውም እጩ ተጋቢ በውሉ መፍረስ የተጐዳው ወገን ሥነ-ሥርዓቱን ለማስፈፀም ያወጣውን ወጪ የመተካትና ለእርሱም ሆነ ለቤተዘመዶቹ የተደረገ ስጦታ ቢኖር የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ጋብቻው ሳይፈፀም የቀረው በበቂና ተቀባይነት ባለው ምክንያት ከሆነ የመተጫጨት ውሉን ቀሪ ያደረገው ወገን ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ወጭና ስጦታ የመመለስ ግዴታ አይኖርበትም፡፡

**አንቀጽ 9 የመቀጮ የውል ቃል ውጤት የሌለው ስለመሆኑ**

በማናቸውም የመተጫጨት ውል ውስጥ ውሉን ባፈረሰው ወገን ላይ ተጨማሪ መቀጮን የሚጥል ድንጋጌ ገብቶ ከሆነ በዚህ ሕግ መሰረት በእጩ ተጋቢዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 10 ስለ ይርጋ**

ከመተጫጨት ውል መፍረስ ወይም አለመከበር ጋር ተያይዞ የሚነሣ ማናቸውም ክርክር የውሉ መጣስ ከተከሰተበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሥልጣን ላለው የዳኝነት አካል ክስ ያልቀረበበት ከሆነ በይርጋ ይታገዳል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለጋብቻ አፈፃፀም
## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**አንቀጽ 11 ትርጓሜ**

ጋብቻ ማለት ለአካለ መጠን የደረሱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለዘለቄታው አብሮ በመኖር ሃሣብ በራሳቸው ነፃ ምርጫ በሕግ ለመዋሐድ ፈቅደው በይፋ የሚመሠርቱት ግንኙነት ወይም በዚሁ ግንኙነታቸው አማካኝነት የሚዋቀር ሕጋዊ ተቋም ነው፡፡

**አንቀጽ 12 ልዩ ልዩ የጋብቻ አፈጻጸም ሥርአቶች**

www.abyssinialaw.com

1. ጋብቻ በአንድ የክብር መዝገብ ሹም ፊት ሊፈፀም ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /1/ የተጠቀሰው ቢኖርም ጋብቻ በተጋቢዎች ሀይማኖት ወይም ባህል መሠረት ሊፈጸም ይችላል፡፡

**አንቀጽ 13 በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈጸም ጋብቻ**

ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ጋብቻ ለመፈጸም ተስማምተው በክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ ፈቃዳቸውን ሲገልጹና የክብር መዝገብ ሹሙም ይህንኑ ፈቃዳቸውን ሲቀበል ነው፡፡

**አንቀጽ 14 በሀይማኖት ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ጋብቻ**

ጋብቻ በሃይማኖትሥርዓት መሠረት ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት በሃይማኖታቸው ወይም ከሁለት በአንዳቸው ሃይማኖት መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው፡፡

**አንቀጽ 15 በባህል ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ጋብቻ**

ጋብቻ በባህል ሥርዓት መሠረት ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት በሚኖሩበት አካባቢ ባህል ወይም በሁለቱ ተጋቢዎች ወይም ከሁለቱ ተጋቢዎች በአንዳቸው ባህል መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው፡፡

**አንቀጽ 16 ከክልሉ ውጭ ስለሚፈጸም ጋብቻ**

1. በተፈፀመበት አካባቢ የጋብቻ አፈፃፀም ሕግ መሠረት ከክልሉ ውጭ ተፈፅሞ የተገኘ ማናቸውም ጋብቻ ይህ ሕግ ለጋብቻ አፈፃፀም የሚጠይቃቸውን አስፈላጊ ሁኔታዎች አሟልቶ መፈፀሙ እስከተረጋገጠ ድረስ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈፀመ ማናቸውም ጋብቻ በዚህ ሕግ ተቀባይነት የሚኖረው የክልሉን ሕዝብ ሞራላዊ እሴት እስካልተቃረነ ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች**

**አንቀጽ 17 ፈቃድ**

የሚፀና ጋብቻ ተፈጸመ የሚባለው ተጋቢዎቹ ለመጋባት ነፃና ሙሉ ፈቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 18 እድሜ**

1. ወንዱም ሆነ ሴቷ አሥራ ስምንት አመት ሣይሞላቸው ጋብቻ መፈጸም አይችሉም፡፡
2. በዚህ አንጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ከባድ ምክንያት ሲያጋጥም ተጋቢዎቹ ራሣቸው ወይም ከተጋቢዎቹ የአንዳቸው ወላጆች ወይም አሣዳሪዎች የሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት የክልሉ ፍትህ ቢሮ ከመደበኛው የጋብቻ እድሜ ከሁለት አመት ያልበለጠ ጊዜ በመቀነስ እንዲጋቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 19 የስጋ ዝምድና**

1. በቀጥታ የስጋ ዘመዶች /በወላጆችና በተወላጆች/ መካከል ጋብቻ መፈጸም ክልክል ነው፡፡
2. ወደ ጎን በሚቆጠር የስጋ ዝምድና፣አንድ ወንድ ከእህቱ ወይም ከአክስቱ እንዲሁም አንዲት ሴት ከወንድሟ ወይም ከአጎቷ ጋር ጋብቻ መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡

**አንቀጽ 20 የጋብቻ ዝምድና**

1. በቀጥታ የጋብቻ ዘመዶች መካከል ጋብቻ መፈጸም ክልክል ነው፡፡
2. ወደጎን በሚቆጠር የጋብቻ ዝምድና፣ባል ከሚስቱ እህት ወይም ሚስት ከባሏ ወንድም ጋር ጋብቻ መፈፀም ክልክል ነው፡፡

**አንቀጽ 21 በሕግ ያልተረጋገጠ ልጅነት**

የአንድ ሰው ተወላጅነት በሕግ መሠረት ያልተረጋገጠ ቢሆንም እንኳን በማህበረሰቡ ዘንድ በተወላጅነት የሚታወቅ ከሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 19 እና 20 እንደተመለከተው ጋብቻን ለማስከልከል በቂ ነው፡፡

**አንቀጽ 22 በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈፀም ስለመከልከሉ**

ማንኛውም ሰው አስቀድሞ በጋብቻ የተሣሠረ ከሆነ ይኸው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሌላ ጋብቻ መፈጸም አይችልም፡፡

**አንቀጽ 23 ጋብቻ በእንደራሴ መፈጸም የማይቻል ስለመሆኑ**

1. ጋብቻ ሲፈጸም ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻው በሚፈጸምበት ጊዜ በግንባር ተገኝተው ፈቃዳቸውን መስጠት አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ከባድ ምክንያት መኖሩን እና በእንደራሴ አማካኝነት ጋብቻውን ለመፈጸም የሚፈልገው ተጋቢ ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ የገለፀ መሆኑን የፍትህ ቢሮው ሲያረጋግጥ ጋብቻው በእንደራሴ ሊፈፀም ይችላል፡፡

**አንቀጽ 24 መሠረታዊ ስህተት**

1. በስህተት በተገኘ ፈቃድ ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻ አይፀናም፡፡
2. በስህተት ምክንያት ፈቃድ ተጓደለ የሚባለው ስህተቱ መሠረታዊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ/2/ የተገለጸው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ መሠረታዊ ስህተት እንዳለ ይቆጠራል፡-
ሀ/ በሚያገባው ሰው ማንነት ላይ በመሣሣቱ ምክንያት አገባዋለሁ ብሎ ያላሰበውን ሠው ያገባ ሲሆን፤
ለ/ የሚያገባው ሰው ሊድን የማይችል ከባድ በሽታ ወይም ለተወላጆች ሊተላለፍ የሚችል ነዋሪ በሽታ ያለትበት መሆኑን ሳያውቅ ያባው ሲሆን፤
ሐ/ ሌላው ተጋቢ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የማይችል መሆኑን ባለማወቁ ምክንያት ያገባው ሲሆን፤
መ/ ሌላው ተጋቢ ከተመሣሣይ ጾታ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የመፈጸም ልምድ ያለው መሆኑን ባለማወቁ ምክንያት ያገባው ሲሆን፡፡

**አንቀጽ 25 በሀይል ሥራ የተገኘ ፈቃድ**

1. በሀይል ሥራ በተገኘ ፍቃድ ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻ አይፀናም፡፡
2. ፈቃድ በሀይል የተገኘ ነው የሚባለው ፈቃዱን የሰጠው ተጋቢ ራሱን ወይም ከወላጆቹ ወይም ከተወላጆቹ አንዱን ወይም ሌላ ለርሱ የቅርብ ዘመድ የሆነን ሰው ሊፈጸምበት ከተቃረበ ከባድ አደጋ ለማዳን ሲል ፈቃዱን የሰጠ ሲሆን ነው፡፡

**አንቀጽ 26 በፍርድ ስለተከለከለ ሰው ጋብቻ**

1. በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር ጋብቻ መፈጸም አይችልም፡፡
2. ስለዚህ ጉዳይ ለፍርድ ቤት የሚቀርበውን ጥያቄ የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሣዳሪው ሊያቀርበው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 27 በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ**

1. አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኂላ አንድ መቶ ሰማኒያ ቀን ካላለፈ በስተቀር እንደገና ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መፈጸም አትችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ሴቲቱ አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኂላ አንድ መቶ ሰማኒያ ቀን ሣይሞላ፡-
ሀ. የወለደች እንደሆነ፣ወይም
ለ. ጋብቻ የምትፈጽመው ከቀድሞ ባሏ ጋር እንደሆነ፣ ወይም
ሐ. እርጉዝ አ ለመሆኗ በህክምና የተረጋገጠ እንደሆነ፣ወይም
መ. በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ እንዳትጠብቅ ፍርድ ቤት የወሰነ እንደሆነ፣በብቸኝነት ለመኖር ስለተወሰነው ጊዜ የተደነገገው ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ክፍል ሶሶት
## ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃወም

**አንቀጽ 28 ስለመቃወም**

ጋብቻ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆነ ሁኔታ አልተሟላም በማለት ሊፈጸም የታሰበ ጋብቻ እንዳይፈጸም ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል፡፡

**አስቀጽ 29 መቃወም ስለሚችሉ ወገኖች**

ጋብቻ እንዳይፈጸም መቃወም የሚችሉ ወገኖች የሚከተሉት ብቻ ናቸው፡-
ሀ. በእድሜ ምክንያት ሲሆን ወላጆች ፣ አቃቤ ህግ ወይም ሌላ ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው፣
ለ. በስጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ሲሆን የተጋቢዎቹ ወይም የአንደኛው ተጋቢ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፣ አሥራ ስምንት አመት የሞላቸው ወንድሞች ወይም እህቶች ወይም አቃብ ህግ፤
ሐ. በጋብቻ ላይ ጋብቻ ሊፈጸም ሲሆን ሌላ ጋብቻ ከሚፈጽመው ሰው ጋር የቀደመ ጋብቻ አለኝ የሚለው ተጋቢ ወይም አቃቤ ህግ፤
መ. በፍርድ በመከልከል ምክንያት ሲሆን አሣዳሪው ወይም ዐቃቤ ህግ፤

**አንቀጽ 30 መቃወሚያ ስለ ሚቀርብበት ሥርዓትና ጊዜ**

1. ጋብቻ እንዳይፈጸም የሚቀርበው መቃወሚያ በጽሁፍ ሆኖ እጅግ ቢዘገይ ጋብቻው ከሚፈጸምበት ከ 15 ቀን በፊት ለጋብቻ አስፈጻሚው ባለስልጣን መቅረብ አለበት፡፡
2. ጋብቻ አስፈጻሚው ባለስልጣን በመቃወሚያው ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት የተጋቢዎቹን አስተያየት መቀበል ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 31 በመቃወሚያው ላይ ስለሚሰጠው ውሣኔ**

1. ጋብቻ የሚያስፈጽመው ባለስልጣን በሚቀርብለት መቃወሚያ ላይ በአምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡
2. ጋብቻ አስፈጻሚው ባለስልጣን መቃወሚያውን ባለመቀበል ጋብቻው እንዲፈጸም የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ የሆናል፡፡
3. ጋብቻ አስፈጻሚው ባለስልጣን መቃወሚያውን የተቀበለው እንደሆነ ጋብቻው እንዳይፈጸም ማድረግ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ የተመለከተው ውሣኔ የተሰጠ እንደሆነ ባለስልጣኑ ለውሣኔው ምክንያት ያደረገውን ጉዳይ ተጋቢዎቹ ወዲያውኑ እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 32 ስለ ይግባኝ**

1. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ /3/ በተመለከተው ሁኔታ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት የጋብቻ አስፈጻሚውን ባለስልጣን ውሣኔ የሻረው እንደሆነ ባለስልጣኑ ጋብቻውን ያስፈጽማል፡፡

**ክፍል አራት**

**በክብር መዝገብ ሹም ፊት ስለሚፈጸም ጋብቻ**

**አንቀጽ 33 ስልጣን ያለው የክብር መዝገብ ሹም**

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ከተጋቢዎቹ ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች አንዱ ጋብቻው ከሚፈጸምበት ጊዜ በፊት ቢያንስ ለስድስት ወራት ያህል ሣይቋረጥ በሚኖርበት ቦታ በሚገኘው የክብር መዝገብ ሹም ፊት ይፈጸማል፡፡

**አንቀጽ 34 ጋብቻ ለመፈጸም ጥያቄ ስለማቅረብ እና ስለሚቀርብበት ጊዜ**

ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈጸም ማሰባቸውን እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን ለመፈጸም ከወሰኑበት ከአንድ ወር በፊት ለክብር መዝገብ ሹሙ ማስታወቅ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 35 ጋብቻ የሚፈጸምበትን ቀን ስለመወሰንና ስለማስታወቅ**

የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄው እንደቀረበለት ከተጋቢዎቹ ጋር በመነጋገር ጋብቻው የሚፈጸምበትን ትክክለኛ ቀን ከወሰነ በኂላ ጋብቻው የሚፈጸምበትን ቀን በመግለጽ አመቺ በሆነው መንገድ ማስታወቂያ ያወጣል፡፡

**አንቀጽ 36 የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓት እና ጋብቻ ው መፈጸሙን ስለማስታወቅ**

1. ጋብቻው ሁለቱ ተጋቢዎች እና ከእያንዳንዱ ተጋቢ በኩል ሁለት ሁለት ምስክሮች በተገኙበት በግልጽ ይፈጸማል፡፡
2. ተጋቢዎችና ምስክሮቹ ጋብቻ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች አለመጣሣቸውን በቃለ መሐላ ያረጋግጣሉ፡፡
3. ተጋቢዎችና ምስክሮቹ የመሐላ ቃል ከመስጠታቸው በፊት የሚሰጡት ቃል ስለሚያስከትለው ኃላፊነት የክብር መዝገብ ሹም በግልጽ ማስረዳት አለበት፡፡
4. ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈጸም መፍቀዳቸውን ለክብር መዝገብ ሹም በግልጽ ያረጋጋጣሉ፡፡
5. ሁለቱም ተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው በክብር መዝገብ ላይ መፈረም አለባቸው፡፡
6. ከዚህ በላይ የተገለጹት ሥርዓቶች የተፈጸሙ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹ በህጋዊ ጋብቻ የተሣሠሩ መሆናቸውን አስታውቆ ለተጋቢዎቹ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡

**ክፍል አምስት**

**ሌሎች የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቶች**

**አንቀጽ 37 በሃይማኖት ሥርዓት የሚፈጸም ጋብቻ**

1. በሀይማኖት ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈጸም የሚችልበትና የአፈጻጸሙ ሥርዓት እንደየ ሃይማኖቱ ይወሰናል፡፡
2. በዚህ ሕግ ለማንኛውም የጋብቻ አፈጻጸም መሟላት አለባቸው የተባሉት ሁኔታዎች በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ለሚፈጸም ጋብቻም መሟላት አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 38 በባህል ሥርዓት ስለሚፈጸም ጋብቻ**

1. በባህል ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈጸም የሚችልበትና የአፈጻጸሙ ሥርዓት በአካባቢው ባህል ይወሰናል፡፡
2. በዚህ ህግ ለጋብቻ አፈጻጸም መሟላት አለባቸው የተባሉት ሁኔታዎች በባህል ሥርዓት መሠረት ለሚፈጸም ጋብቻም መሟላት አለባቸው፡፡

**ክፍል ስድስት**

**ስለ ጋብቻ ምዝገባ**

**አንቀጽ 39 ጋብቻን ስለማስመዝገብ**

1. ጋብቻው የተፈጸመው በማንኛውም የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓት ቢሆንም አግባብ ባለው የክብር መዝገብ ሹም መመዝገብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ምዝገባውን ያከናወነ የክብር መዝገብ ሹም ለተጋቢዎቹ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
3. ማንኛውም ጋብቻ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ውጤት ይኖረዋል፡፡

**አንቀጽ 40 የጋብቻ መዝገብ ስለማደራጀት**

1. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ያላስመዘገቡ ቢሆንም እንኳ የክብር መዝገብ ሹም ጋብቻ መፈጸሙን ያወቀ እንደሆነ የጋብቻ መዝገብ በስልጣኑ ያደራጃል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. ይህ በሚሆንበት ጊዜ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹና እንደ ነገሩ ሁኔታ ምስክሮቻቸው ቀርበው በጋብቻው መዝገብ ላይ እንዲፈርሙ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 41 የጋብቻ መዝገብ ይዘት**

የጋብቻ መዝገብ የሚያመለክተው፣

ሀ. የተጋቢዎችን ሙሉ ስም፣የተወለዱበትን ቀን ቦታና ፣የመኖሪያ አድራሻቸውን፤

ለ. የምስክሮችን ሙሉ ስም፣የተወለዱበትን ቀን፣ቦታና የመኖሪያ አድራሻቸው፤

ሐ. ጋብቻው የተፈጸመበትን ሥርዓት ፣ ቀንና ቦታ እንዲሁም የተመዘገበበትን ቀን ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት

**አንቀጽ 42 የእድሜ ሁኔታ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ /2/ የተደነገገው እንተደጠበቀ ሆኖ እድሜአቸው ከአሥራ ስምንት አመት በታች በሆኑ ሰዎች መካከል የተፈጸመ ጋብቻ በማንኛውም ባለጉዳይ ወይም በአቃቤ ሕግ ጥያቄ እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡
2. ሕጉ የሚጠይቀው የጋብቻ እድሜ ከተሟላ በኋላ ጋብቻው አንዲፈርስ ጥያቄ ማቅረብም ሆነ መወሰን አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 43 የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና**

በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ጋብቻ እንዳይፈጸም የተደነገገውን ክልከላ በመተላለፍ የተፈጸመ ጋብቻ በማንኛውም ባለጉዳይ ወይም በአቃቤ ህግ ጥያቄ እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 44 በጋብቻ ላይ ጋብቻ**

1. በጋብቻ ላይ ሌላ ጋብቻ ተፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ በመጀመሪያው ወይም በሁለተኛው ተጋቢ ወይም በአቃቤ ህግ ጥያቄ የኂለኛዉ ጋብቻ እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡
2. ሆኖም የመጀመሪያው ተጋቢ የሞተ እንደሆነ የኂላኛው ጋብቻ እንዲፈርስ መጠየቅ አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 45 በፍርድ ክልከላ ምክንያት ጋብቻን ስለማፍረስ**

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው ፍርድ ቤት ሣይፈቅድ ጋብቻ ፈጽሞ የተገኘ እንደሆን የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሣዳሪው ጋብቻው እንዲፍርስ ጥያቂውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የተከለከለው ሰው ጋብቻው እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ክልከላው ከቀረበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወር ካለፈ በኂላ ሊቀርብ አይችልም፡፡
3. ጋብቻው እንዲፈርስ በአሣዳሪው ወይም በአቃቤ ሕግ የሚቀርበው ጥያቄ ጋብቻው መፈጸሙን ከአወቀ ከስድስት ወር በኂላ ወይም በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ክልከላው ከቀረ በኂላ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 46 በሃይል ተግባር የተፈጸመን ጋብቻ ስለማፍረስ**

1. ማንኛውም ሰው ተገዶ ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ስለዚሁ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ የሃይል ሥራው ከቀረበበት ከስድስት ወር በኂላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈጸመ ከሁለት አመት በኂላ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 47 በስህተት ምክንያት የተፈጸመን ጋብቻ ስለማፍረስ**

1. ማንኛውም ሰው ከመሠረታዊ ስህተት በመነሣት ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅርብ ይችላል፡፡
2. ስለዚሁ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ መሣሣቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኂላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈጸመ ከሁለት አመት በኂላ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 48 በብቸኝነት ለመኖር የተወነውን ጊዜ ስላለመጠበቅ**

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተውና በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነው ጊዜ አልተከበረም በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 49 የክብር መዝገብ ሹም ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ**

ጋብቻውን ያስፈጸመው የክብር መዝገብ ሹም በዚህ ሕግ በአንቀጽ 34 መሠረት ስልጣን አልነበረውም በማለት ብቻ ጋብቻው እንዲፈርስ ለመጠየቅ ወይም ለመወሰን አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 50 የስነ - ሥርዓት አለመጠበቅ**

በዚህ ህግ በአንቀጽ 36 /3/ እና /6/ የተመለከቱት ሥርዓቶች አልተጠበቁም በማለት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ሊወሰን አይችልም፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የጋብቻ ውጤት

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**አንቀጽ 51 ሁሉም የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቶች ተመሣሣይ ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ**

www.abyssinialaw.com

1.በማናቸውም አይነት የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓት መሠረት የተፈጸመ ቢሆንም ማንኛውም ጋብቻ ተመሣሣይ ህጋዊ ውጤት ይኖረዋል፡፡
2.በዚህ ረገድ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ወይም በሃይማኖት ወይም በባህል በታዘዙት ሥርዓቶች መሠረት የተፈጸመ ቢሆንም ልዩነት አይደረግበትም፡፡

**አንቀጽ 52 የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም**

የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በእውነት መፈጸሙን ወይም ተፈጽሟል ተብሎ መገመቱ ጋብቻው ለሚያስከትለው ውጤት አስፈላጊ አይደለም፡፡

**አንቀጽ 53 /1 / የጋብቻ ውል**

1. ተጋቢዎቹ ጋብቻቸው ንብረታቸውን በተመለከተ ስለሚያስከትለው ውጤት ጋብቻቸውን ከመፈጸማቸው በፊት ወይም እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት እለት በውል መወሰን ይችላሉ፡፡
2. እንዲሁም ግላዊ ግንኙነታቸውን በሚመለከት የሚኖሯቸውን መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ውል መወሰን ይችላሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ መሠረት ተጋቢዎቹ የሚያደርጓቸው ውሎች አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 54 /2/ የተጋቢዎቹ ችሎታ ማጣት**

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው የሚያደርገውን የጋብቻ ውል እርሱ እራሱ ካልፈጸመውና ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም፡፡
2 በሕግ የተከለከለ ሰው ቢሆንም እንኳ የጋብቻ ውል መዋዋልን በተመለከተ ችሎታ እንዳለው ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 55 /3/ የውሉ ፎርም**

የጋብቻ ውል በጽሁፍ ካልተደረገና አራት ምስክሮች ሁለት በባል ወገን ሁለት በሚስት ወገን የፈረሙበት ካልሆነ በስተቀር ውጤት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 56 /4/ የውሉ ሰነድ ስለሚቀመጥበት ቦታ**

1. የጋብቻ ውሉ ሰነድ ለሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በማስረጃነት የሚሰጣቸው ሲሆን አንድ ቅጅ ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው የፍትህ አካል ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ይቀመጣል፡፡
2. ተጋቢዎች ወይም ከተጋቢዎች አንዱ ለማየት በፈለጉ ጊዜ እንዲሁም በፍርድ ቤት ወይም ከተጋቢዎቹ በአንዱ የተፈቀደላቸው ሰዎች የውሉን ሰነድ ለማየት ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 57 /5/ ውል ለመዋዋል ስላለው የነፃነት ወሰን**

1. ተጋቢዎች በጋብቻቸው ውል ውስጥ በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታን የሚያስከትሉ ስምምነቶችን ማድረግ አይችሉም፡፡
2. እንዲሁም ተጋቢዎቹ ባህልን ወይም ሃይማኖትን ወይም የአንድን አገር ሕግ በጥቅሉ በመጥቀስ ብቻ ተስማምተናል በማለት የሚያደርጉት የጋብቻ ውል ውጤት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 58 /6/ የጋብቻ ውልን ስለማሻሻል**

1. የጋብቻ ውል እንዲሻሻል የቤተሰቡ ጥቅም የሚጠይቅ ሲሆንና ተጋቢዎቹ ራሳቸው ሲስማሙ ውሉን በማሻሻል ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው የፍትህ አካል እንዲያፀድቅላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተጠቀሰው አካልም በተጋቢዎቹ ተሻሽሎ የቀረበው የጋብቻ ውል የቤተሰቡን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተሻሻለውን ውል ተቀብሎ ያፀድቃል፣ ይመዘግባል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር በተመለከተው ሁኔታ ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው የፍትህ አካል ውሉን ተቀብሎ ያፀደቀው እንደሆነ ይኸው የተሻሻለው የጋብቻ ውል በዚሁ አካል ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ተመዝግቦ ይቀመጣል፡፡

**አንቀጽ 59 /7/ የሕግ ተፈጻሚነት**

የጋብቻ ውል በሌለ ጊዜ ወይም የጋብቻ ውል ቢኖርም በሕግ ሣይፀና የቀረ እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱን ድንጋጌዎች ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት

**አንቀጽ 60 መከባበር፣ መተጋገዝና መደጋገፍ**

1. ባልና ሚስት እርስ በእርሣቸው መከባበር መተጋገዝና መደጋገፍ አለባቸው፡፡
2. በጋብቻው ውል ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 61 የቤተሰብ የጋራ አመራር**

**1. ጠቅላላ**

1. በቤተሰብ አመራር ረገድ ባልና ሚስት እኩል መብት አላቸው፡፡
2. ባልና ሚስቱ በማናቸውም ረገድ የቤተሰቡን ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ ልጆቻቸውን በመልካም ስነምግባር ታንጸው እንዲያድጉ፣ ተገቢ ትምህርት እንዲቀስሙና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲገነቡ ለማድረግ መተባበር አለባቸው፡፡

www.abyssinialaw.com

**አንቀጽ 62**

**2. ከተጋቢዎች አንዱ ቤተሰቡን ለመምራት ስላለመቻሉ**

1. ከባልና ሚስት አንደኛው ችሎታ ያጣ፣የጠፋ ወይም ቤተሰቡን ጥሎ የሄደ ወይም ከመኖሪያ ስፍራው በመራቁም ሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት ፈቃዱን ለመስጠት በማይችልበት ሁኔታ በሚገኝበት ጊዜ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 61 ሥር የተመለተውን የቤተሰብ አመራር አንደኛው ተጋቢ ብቻውን ይፈጽማል፡፡
2. ባልና ሚስት በጋብቻ ውላቸው ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 63 ከጋብቻ በፊት ከሌላ ስለተወለዱ ልጆች**

1.ከባልና ከሚስቱ አንዱ ከጋብቻ በፊት ከሌላ የወለዳቸውን ልጆች መልካም አስተዳደግ በሚመለከት በራሱ አሣብና መሪነት የፈቀደውን ውሣኔ ለማድረግ ሙሉ መብት ይኖረዋል፡፡

2. ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 64 አብሮ መኖርና የሩካቤ ስጋ ግንኙነት**

1. ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ ይገደዳሉ፡፡
2. ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስት ከጋብቻ የሚጠበቀውንና ደንበኛውን የሩካቤ ስጋ ግንኙነት መፈጸም አለባቸው፡፡
3. ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 65 የመኖሪያ ስፍራን ስለመወሰን**

ባልና ሚስት የሚኖሩበትን ስፍራ በጋራ ይወስናሉ፡፡

**አንቀጽ 66 በስምምነት ተለያይቶ ስለመኖር**

1. በዚህ ሕግ በአንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የተመለከተው ቢኖርም ባልና ሚስቱ ለተወሰነ ጊዜ ተለያይተው ለመኖር መስማማት ይችላሉ፡፡
2. ስለዚሁ ጉዳይ የተደረገውን ስምምነት መለወጡ የማይገባ ካልሆነ በስተቀር ከሁለቱ ተጋቢዎች አንደኛው አስቦ ሊሰርዘው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 67 የመተማመን ግዴታ**

ባል ለሚስቱ ሚስት ለባልዋ ታማኝ የመሆን ግዴታ አለባቸው፡፡

**ክፍል ሶስት**

## ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት

**አንቀጽ 68 የባልና ሚስት የግል ሀብት**

**1.ያለግብይት የተገኙ ንብረቶች**

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግላቸው የነበሩዋቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኙዋቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው ይቀራሉ፡፡

**አንቀጽ 69 /2/ በግብይት የተገኙ ንብረቶች**

1.ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንደኛው የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት በለውጥ ያገኘው በግል ገንዘቡ የገዛው ወይም የግል ንብረቱን ሽጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል፡፡

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብ እና ፍርድ ቤት ተቀብሎ ሲያፀድቀው ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 70 የግል ሀብትን ስለማስተዳደር**

1. ***መሠረቱ***

1. እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ለማስተዳደርና ገቢውንም ለመቀበል ይችላል፡፡
2. እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ሊያዝበት ነፃነት አለው፡፡

**አንቀጽ 71 /2/ የግል ሀብት አስተዳደርን በጋብቻ ውል ስለመወሰን፤**

1. ከባልና ሚስት አንደኛው የሌላውን ተጋቢ የግል ሀብት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት እና እንደአስፈላጊነቱም እንዲያዝዝበት በጋብቻ ውላቸው ሊወስኑ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተው አኳኋን ንብረት የማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው ተጋቢ በሌላኛው ተጋቢ ሲጠየቅ ስለንብረቱ አስተዳደር አመታዊ የሂሣብ መግለጫ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 72 /3/ ስለ ውክልና ስልጣን**

ከተጋቢዎች አንዱ የግል ሀብቱን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት ለሌላኛው ተጋቢ ውክልና መስጠት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 73 የባልና ሚስት የጋራ ሃብት**

1. ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያስገኙዋቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ፡
2. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በስተቀር ባልና ሚስቱ ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል፡፡

www.abyssinialaw.com

3. በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው ቃል በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር በስጦታ ወይም በኑዛዜ ለተጋቢዎቹ የተሰጧቸው ንብረቶች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 74 የሕግ ግምት**

1. አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳ የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
2. የግል ንብረት መሆኑን ሶሶተኛ ወገኖች የሚያውቁ ወይም ሊያውቁት የሚገባ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዱ የኽው ንብረት የግል ነው በማለት በሶስተኛ ወገን ላይ መቃወሚያ አድርገው ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 75 ስለባልና ሚስቱ ገቢ**

**1. መደበኛ የገቢ አስተዳደር**

1. ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው ገቢያቸውን በየራሣቸው ይቀበላሉ፡፡
2. ባልና ሚስት በየግላቸው የሚያገኙትን ገቢ የግል ወይም የጋራ የባንክ ሂሣብ በመክፈት ማስቀመጥ ይችላሉ፡፡
3. ከባልና ከሚስት አንደኛው ሲጠይቅ ሌላኛው ተጋቢ ያገኙውን የገቢ መጠን የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 76 /2/ ልዩ ሁኔታ**

1. ከባልና ከሚስት አንዱ ገቢውን ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበልለት ሥልጣን ለመስጠት ሙሉ ነፃነት አለው፡፡
2. ከባልና ከሚስት በአንደኛው ጠያቂነት የአንደኛውን ገቢ ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበልና ለመቀበሉም ደረሰኝ እንዲሰጥ ፍ/ቤት ሊወስን ይችላል፡፡
3. በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ከባልና ከሚስት የአንደኛው ገቢ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከበር በፍርድ ቤት ሊታዘዝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 77 የጋራ ሀብትን ስለማስተዳደር**

1. ከባልና ከሚስት አንዱ የጋራ ሀብታቸውን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድር ግልጽ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ባልና ሚስቱ የጋራ ሀብታቸውን በጋራ ያስተዳድራሉ፡፡
2. ከባልና ከሚስት አንዱ ችሎታ የለውም ተብሎ ሲወሰን ወይም ንብረት የማስተዳደር መብቱን ሲገፈፍ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የጋራ ሀብታቸውን ለማስተዳደር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ሌላኛው ተጋቢ የጋራ ሀብታቸውን የማስተዳደሩን ተግባር ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ 78 የማስታወቅ ግዴታ**

ከተጋቢዎች አንዱ ብቻ የጋራ ሀብታቸውን በሚያስተዳድርበት ጊዜ የሀብቱን አስተዳደር በተመለከተ ለሌላኛው ተጋቢ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 79/1/ የተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ**

በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ ነው፤

ሀ. የጋራ የሆነውን የማይንቀሣቀስ ንብረት ለመሸጥ፣ለመለወጥ፣ለማከራየት፣በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ በዚሁ ንብረት ላይ ሌሎች ሰዎች መብት እንዲያገኙ ለማድረግ፤

ለ. ዋጋቸው ከብር 500/አምስት መቶ/ በላይ የሆኑ የሚንቀሳቀሱ የጋራ ንብረቶችን ወይም የገንዘብ ሰነዶችን፣ለመሸጥ፣ለመለወጥ፣በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ለማስተላለፍ ፤

ሐ. ከብር 100/አንድ መቶ/ በላይ ዋጋ ያለውን የጋራ ንብረት ወይም ገንዘብ ለሌላ ሰው በስጦታ ለማስተላለፍ፤

መ. ከብር 500/አምስት መቶ/ በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ ሠው ዋስ ለመሆን፡፡

**አንቀጽ 80 /2/ የስምምነቱ አለመኖር ስለሚያስከትለው ውጤት**

1. አንደኛው ተጋቢ ከዚህ በላይ የተመለተውን ድንጋጌ ባለማክበር የውል ግዴታ ገብቶ የተገኘ እንደሆነ ሌላኛው ተጋቢ ለፍርድ ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ ግዴታው ሊፈርስ ይችላል፡፡
2. ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው መገባቱን ከአወቀበት ጊዜ ጀምሮ ከስድስት ወር በኂላ ወይም በሌላ በማናቸዉም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኂላ ሊቀርብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 81 የባልና ሚስት እዳ**

1. ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ እዳ ከባለእዳው ተጋቢ የግል ሀብት፤የግል ሀብቱ እዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ደግሞ ከጋራ ሀብታቸው ይከፈላል፡፡
2. እዳው የመጣው ለትዳራቸው ጥቅም ከሆነ ከጋራ ሀብታቸው፤የጋራ ሀብታቸው እዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ደግሞ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሀብት ይከፈላል፡፡

**አንቀጽ 82 ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ የሚቆጠር እዳ**

የሚከተሉት እዳዎች ለትዳር ጥቅም እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

ሀ. ለባልና ለሚስት እንዲሁም ለልጆቻቸው የእለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማሟላት

www.abyssinialaw.com

የተገቡ እዳዎች፤

ለ. ባል ወይም ሚስት ቀለብ ለመስጠት ያለባቸው ግዴታ ለመወጣት የተደረጉ ወጭዎች፤

ሐ. ከባልና ከሚስት በአንደኛው ወይም በእዳ ጠያቂው አመልካችነት ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ ፍርድ ቤት የተቀበለው ሌላ ማናቸውም እዳ፡፡

**አንቀጽ 83 የትዳር ወጪዎችን ስለመሸፈን**

ተጋቢዎች የትዳራቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና እንዳየችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 84 በተጋቢዎች መካከል ስለሚደረጉ ውሎች**

ባልና ሚስቱ ተጋብተው በሚኖሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሚያደርጓቸው ውሎች ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው የፍትህ አካል ካላፀደቃቸው በስተቀር ውጤት አይኖራቸውም፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ስለ ጋብቻ መፍረስ

**አንቀጽ 85 በማናቸውም አይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት**

**የተቋቋሙ ጋብቻዎች እኩል ስለመሆናቸው**

1. ጋብቻው የተፈጸመበት ሥርዓት ማናቸውም አይነት ቢሆን የጋብቻው መፍረስ የሚያስከትለው ውጤት አንድ አይነት ነው፡፡
2. ጋብቻው የተፈጸመው በማናቸውም የጋብቻ አፈጻጸም ሥርአት ቢሆንም እንኳ የጋብቻውን መፍረስ በተመለከተ ማናቸውም ዓይነት ልዩነት አይደረግም፡፡

**አንቀጽ 86 ጋብቻ ስለሚፈርስባቸው ምክንያቶች**

ጋብቻ የሚፈርሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡፡

ሀ. ከተጋቢዎቹ አንዱ ሲሞት ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሣኔ ሲሰጥ፤ ወይም

ለ. ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት በሕግ መሠረት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን፤ ወይም

ሐ. የፍች ውሣኔ ሲሰጥ፡፡

**አንቀጽ 87 ፍች ስለሚወሰንበት ሁኔታ**

ጋብቻ በፍች እንዲፈርስ ሊወሰን የሚችው፡፡

ሀ. ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሲወስኑና ይህንኑ ለፍርድ ቤት አቅርበው ውሣኔያቸው ተቀባይነት ሲያገኝ ፤ወይም

ለ. ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት ጋብቻቸው በፍች እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው፡፡

## ክፍል አንድ

## በስምምነት ስለመፋታት

**አንቀጽ 88 በስምምነት ለመፋታት ስለሚቀርብ ጥያቄ**

1. ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታታ የወሰኑ እንደሆነ የፍች ስምምነታቸውንና ፍችው የሚያስከትለውን ውጤት በጽሁፍ አድርገው ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፍችው እንዲፀድቅላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ቢኖርም ተጋብተው ስድስት ወር ያልሞላቸው ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት አይፈቀድላቸውም፡፡
3. ባልና ሚስት ለፍርድ ቤት በሚያቀርቡት የፍች ስምምነት ላይ ለመፋታታ የወሰኑበት ምክንያት እንዲገልጹ አይገደዱም፡፡

**አንቀጽ 89 የፍርድ ቤቱ ስልጣን**

1. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተለው ድንጋጌ መሠረት የመፋታት ጥያቄ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠል ወይም በአንድ ላይ በማስቀረብ ስለጥያቄአቸው ያነጋግራቸዋል፤እንዲሁም የመፋታት ሃሣባቸውን እንዲለውጡ ይጠይቃቸዋል፡፡
2. ባልና ሚስቱ የመፋታት ሀሳባቸውን የማይለውጡ መሆኑን የገለጹ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ከሶሶት ወር የማይበልጥ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ፍላጐታቸውን መሰረት አድርጐ በሚከናወን ምርጫ አግባቢ ሽማግሌዎችን በመሰየም ሊያሰናብታቸው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 90 ጉዳዩን እንደገና ስለማንቀሣቀስ**

1. ባልና ሚስቱ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተው የማሰላሰያ ጊዜ ቢሰጣቸውም እንኳ በመፋታት ሃሣባቸው የፀኑ እንደሆነ የተሰጣቸው የማሰላሰያ ግዜ ከአበቃበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጉዳያቸውን እንደገና በማንቀሣቀስ የፍች ስምምነታቸውን እንዲያፀድቅላቸው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቅጽ /1/ ሥር የተመለተው የስድስት ወር ጊዜ ገደብ ቢኖርም እንኳን ባልና ሚስቱ አዲስ የፍች ስምምነት ከማቅረብ የሚያግዳቸው አይሆንም፡፡

**አንቀጽ 91 የፍች ስምምነቱን ስለማጽደቅ**

www.abyssinialaw.com

1. ፍርድ ቤቱ የፍች ስምምነቱን የሚያፀድቀው የባልና ሚስቱ ትክክለኛ ፍላጎት መሆኑንና ባልና ሚስቱ ፈቃዳቸውን በነፃ የሰጡ መሆኑን፣እንዲሁም ስምምነቱ ከህግና ከሞራል ጋር የማይቃረን መሆኑን ሲያምን ብቻ ነው፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የፍችውን ስምምንት ያፀደቀው እንደሆነ ስለፍችው ዉጤት ያደረጉትንም ስምምነት አብሮ ያፀድቃል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/2/ የተመለከተው ቢኖርም ባልና ሚስቱ ስለፍችዉ ውጤት ያደረጉት ስምምነት የልጆቻቸውን ደህንነትና ጥቅም በበቂ ሁኔታ የማያስጠብቅ ወይም የአንደኛው ተጋቢ ወገን ጥቅም የሚጐዳ ሆኖ ካገኘው ፍርድ ቤቱ የፍችውን ስምምነት ብቻ በማጽደቅ የፍችውን ውጤት በተመለከተ ጉድለቶቹ እንዲስተካከሉ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ</u>

### <u>አንቀጽ 92/1/ የፍች ጥያቄ ስለማቅረብ</u>

1. ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
2. ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን የፍች ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍችውን ለመጠየቅ ምክንያት የሆናቸውን ጉዳይ መግለጽ ይችላሉ፡፡

### <u>አንቀጽ 93 /2/ የፍርድ ቤት ስልጣን</u>

1. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 92 መሠረት ጋብቻው በፍች እንዲፈርስ ጥያቄ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠልም ሆነ በአንድነት በማነጋገር የፍችው ጥያቄ የሚቀርበትንና አለመግባባታቸውን በስምምነት ለመፍታት የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲችሉ ያግባባቸዋል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተው መሠረት ሞክሮ ተፈላጊውን ውጤት ያላገኘ እንደሆነ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ውጤት የማያገኝ መስሎ የታየው እንደሆነ ባልና ሚስቱ ከፍርድ ቤት ውጭ ራሣቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካኝነት ጉዳያቸውን በእርቅ እንዲጨርሱ ሊጠይቃቸው ይችላል፡፡
3. ባልና ሚስቱ ጉዳያቸውን በሽማግሌዎች አማካይነት በእርቅ ለመጨረስ ያልተስማሙ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከሶሶት ወር ያልበለጠ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ያሰናብታቸዋል፡፡
4. ከዚህ በላይ በተመለቱት ድንጋጌዎች መሠረት ተገቢውን ሁሉ አድርጐ ጥረቱ ውጤት ያላስገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የአስታራቂ ሽማግሌዎች ሪፖርት ከደረሰው ወይም እንደሁኔታው ለተጋቢዎቹ የተወሰነው የማሰላሰያ ጊዜ ከአበቃበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የፍች ውሣኔ ይሰጣል፡፡
5. የፍች አቤቱታው እንደቀረበለት ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ባልና ሚስቱ ስለሚተዳደሩበትና ስለሚኖሩበት ሁኔታ፣ስለልጆቻቸው አጠባበቅ፣ስለሚኖሩበት ስፍራና ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ስለንብረታቸው አስተዳደር ተገቢ መስሎ የታየውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
6. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /5/ በተመለከተው መሠረት ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከሁለቱ ተጋቢዎች የአንዳቸው ከጋራ መኖሪያቸው መውጣት የግድ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የጋራ መኖሪያቸውን ለቅቆ ቢወጣ የባሰ ጉዳት የሚደርስበት ወገን የትኛው መሆኑንና እንዲሁም የልጆቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ አመች የሚሆነውን ሁኔታ ሁሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

### አንቀጽ 94 የፍች ውጤቶችን ስለመወሰን

1. በዚህ ክፍል መሠረት ጋብቻው በፍች የፈረሰ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ፍችው ስለሚያስከትለው ውጤት እንዲስማሙ ባልና ሚስቱን ይጠይቃቸዋል፡፡
2. ባልና ሚስቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለመስማማት ያልፈለጉ ወይም ለመስማማት ሞክረው ስምምነት ላይ ለመድረስ ያልቻሉ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በራሱ ወይም በሽማግሌዎች ወይም ፍርድ ቤቱ በሚሾማቸው ባለሙያዎች አማካይነት ወይም አመች መስሎ በሚታየው በማናቸውም ዘዴ የፍችውን ውጤት ይወስናል፡፡
3. የፍችው ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማግሌዎች ወይም በባለሙያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሣኔው ተፈጻሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡
4. ፍርድ ቤቱ ፍችውን አስቀድሞ በመወሰን የፍችውን ውጤት በተመለከተ የሚሰጠውን ውሣኔ እንደሁኔታው ከፍች በኂላ ከ6 ወር ሳልበለጠ ጊዜ ሊያዘገየው ይችላል፡፡

### <u>አንቀጽ 95 ስለ ካሣ</u>

ከባልና ከሚስት አንዱ ለፍችው ምክንያት የሆነውን በደል ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ ለፍትህ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሌላው ተጋቢ ላይ ለደረሰው ጉዳት በዳዩ ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ እንዲከፍል ሊወስን ይችላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ስድስት</u>

## <u>የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት</u>

### <u>አንቀጽ 96 የባልና ሚስትን ሀብት በስምምነት ስለማጣራት</u>

1. በዚህ ሕግ ስለ ካሣ ክፍያ የተፃፋት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጋብቻው በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የፈረሰ እንደሆነ ባልና ሚስቱ የጋብቻቸው መፍረስ በንብረት በኩል የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክተው በሚያደርጉት ስምምነት ወይም በጋብቻ ውላቸው መሠረት ይጣራል፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው የጋብቻ ውል ወይም ስምምነት የሌለው ወይም በሕግ ፊት የማይፀና ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ጋብቻው የተፈፀመበት ሥርዓት ልዩነትን ሣያስከትል የባልና ሚስት ሀብት በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሠረት ይጣራል፡፡

**አንቀጽ 97 የግል ሀብትን መልሶ ስለመውሰድ**

1. ባል ወይም ሚስት የግሉ መሆኑን በማስረዳት የግል ሀብቱ የሆነውን ንብረቱን መልሶ የመውሰድ መብት ይኖረዋል፡፡
2. ከባልና ሚስቱ አንደኛው የግል ሀብት የሆነ ማናቸውም ንብረት ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑንና ከዚሁ ግብይት የተገኘውን ገንዘብ ከጋራ ሃብታቸው ጋር የተቀላቀለ መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ከዚሁ ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት ከጋራ ሀብታቸው በቅድሚያ የማንሣት መብት ይኖረዋል፡፡
3. ባልና ሚስት የየግል ሀብታቸውን የሚያነሱበት ሁኔታ ሲኖር ሁለቱም በመጨረሻ ከተገኘው የንብረት መጠን ላይ እንደየአስተዋጽኦቸው ሊደርሣቸው የሚችለውን ያህል የማንሣት መብት ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ 98 ስለ ካሣ**

1. በዚህ ሕግ መሠረት የጋራ ንብረታቸውን ወይም የሌላኛውን ተገቢ ንብረት በብቸኝነት እንዲያስተዳድር ስልጣን የተሰጠው ተጋቢ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ በፈጸማቸው ድርጊቶች ምክንያት ወይም ከብልሹ አስተዳደር የተነሣ ወይም የካሣ ጠያቂውን መብት በማታለል ድርጊቱ የጎዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በተበዳዩ ወገን ጥያቄ ሲቀርብለት ተገቢ የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው ሊያዝ ይችላል፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ/1/ መሠረት የሚቀርበው የካሣ ጥያቄ ተፈጸመ የተባለው ድርጊት ጋብቻው ከመፍረሱ ከአምስት አመት በፊት ተፈጽሞ እንደሆነ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 99 ያለአግባብ ስለመበልፀግ**

ባልና ሚስት ተቃራኒ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር ከባልና ከሚስት የአንደኛው የግል ሀብት ከሆነ ንብረት የሌላቸው የግል ሀብት ወይም የጋራ ሀብታቸው ያለአግባብ መበልፀጉን ያስረዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ካሣ እንዲከፍለው ሊያዝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 100 የእዳ ጠያቂዎችን መብት ስለማክበር**

ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በጋራ በፍርድ የተረጋገጠባቸው ወይም ሁለቱም ያመኑበት እዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ ይኸው እዳ የባልና ሚስቱ ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ የሚከፈል ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 101/1/ የጋራ ሀብትን ስለማከፋፈል**

ከዚህ በላይ የተመለከቱትና የባልና ሚስት ሀብትን በስምምነት ስለማከፋፈል የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም ተጋቢዎች እኩል የሚከፋፈል ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 102 /2/ የባልና ሚስት ሀብት በአይነት የሚከፋፈል ስለመሆኑ**

1. በመሠረቱ እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ የጋራ ሀብቱ በዓይነት እንዲከፋፈል ይደረጋል፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ/1/ በተመለከተው አኳኋን እኩል ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ልዩነቱ የገንዘብ እንዲካካስ ይደረጋል፡፡
3. የሀብት ክፍፍሉ በሚደረግበት ጊዜ እያንዳንዱ ተጋቢ ይበልጥ ጠቃሚነት ያላቸውን ንብረቶች አንዲያገኝ ለማድረግ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 103 ለማከፋፈል አዳጋች ስለሆኑ ንብረቶች**

1. ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነና ባልና ሚስቱን ንብረቱ ከሁለቱ ለአንዳቸው እንዲሰጥ ለማስማማት ሣይቻል የቀረ እንደሆነ ንብረቱ ተሽጦ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉት ይደረጋል፡፡
2. ስለአሻሻጡ ሁኔታ ባልና ሚስቱ ሣይስማሙ ቀርተው አንደኛው ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ሽያጩ የሚደረገው በጨረታ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 104 ጋብቻው ከፈረሰ በኂላ ከባልና ሚስት ስለሚጠየቅ እዳ**

1. ጋብቻው ከፈረሰና የባልና ሚስት ሀብት ከተከፋፈለ በኌላ የሚጠየቅ ማናቸውም እዳ በጋራ መከፈል የነበረበት በሆነ ጊዜ ስለእዳው አከፋፈል ሁለቱም በየድርሻቸው መጠን ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡
2. እዳው የሚመለከተው አንደኛውን ተጋቢ በሆነ ጊዜ የእዳው ክፍያ ሊጠየቅ የሚችለው ባለእዳ ከሆነው ተጋቢ ብቻ የሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## ጋብቻ ለመፈጸሙ ስለሚቀርብ ማስረጃ

**አንቀጽ 105 የጋብቻ ምስክር ወረቀት**

1. ጋብቻ መፈጸሙን ለማስረዳት የሚቻለው ጋብቻው በተፈጸመበት እለት ወይም ከዚያ በኂላ በሕጉ መሠረት ተዘጋጅቶ በክብር መዝገብ ሹም የተሰጠውን የጋብቻ ምስክር ወረቀት በማቅረብ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

2. በዚህ ሕግ መሰረት የክብር መዝገብ ሹም ተደራጅቶ ሥራውን እስኪጀምር ድረስ በከተማና በገጠር ቀበሌ አስተዳደሮች ሊያዙና ሊጠበቁ ስልሚገባቸው የጋብቻ አስረጅ ሰነዶች አይነትና ዝርዝር የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ሊያወጣና በስራ ላይ ሊያውል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 106 የጋብቻ ምስክር ወረቀት በሌላ ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ**

የጋብቻ ምዝገባ ሣይደረግ የቀረ ወይም መዝግቡ በመጥፋቱ ምክንያት ጋብቻ መፈጸሙን በጋብቻ የምሥክር ወረቀት ለማስረዳት ያልተቻለ እንደሆነ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ጋብቻ መፈፀሙን ማስረዳት ይቻላል፡፡

**አንቀጽ 107 የትዳር ሁኔታ መኖር**

1. **ትርጓሜ**

አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት የትዳር ሁኔታ አላቸው የሚባሉት እራሣቸውን እንደ ባልና ሚስት የሚቆጥሩና የሚኖሩ ከመሆናቸውም በላይ ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደ ባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሆነው ሲገኙ ነው፡፡

**አንቀጽ 108 /2/ ጋብቻ ለመፈጸሙ የትዳር ሁኔታ መኖርን ስለማስረዳት**

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረትአንድ ሰው በራሱና ከእርሱ ጋር ጋብቻ አለኝ በሚለው ወገን መካከል የትዳር ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተውን ግምት ጋብቻው አለመፈጸሙን የሚያሳይ ማናቸውንም አይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ለማፍረስ ይቻላል፡፡

**ምዕራፍ ስምንት**

**ጋብቻ ሣይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር**

**አንቀጽ 109 1. ትርጉም**

ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ማለት አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሕግ በሚፀና አኳኋን ጋብቻ ሣይፈጽሙ በትዳር መልክ የኖሩ ሲሆን ነው፡፡

**አንቀጽ 110 2 . ማብራሪያ**

1. ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው ኖሩ ለማለት ወንድየውና ሴትየዋ የሚያሣዩት ሁኔታ በሕግ እንደተጋቡ ሰዎች አይነት መሆኑ አስፈላጊና በቂ ነው፡፡
2. ለሶስተኛ ወገኖች እንደተጋቡ ሆነው መቅረባቸው አስፈላጊ አይደለም፡፡
3. አንድ ወንድና አንዲት ሴት በታወቀና በተደጋገመ ሁኔታ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸማቸው ብቻ በሁለቱ መካከል ጋብቻ ሣይፈጸም እንደ ባልና ሚስት ያለ ግንኙነት አላቸው ለማለት በቂ ምክንያት አይደለም፡፡

**አንቀጽ 111 የጋብቻ ዝምድናን የማያስከትል ስለመሆኑ**

1. ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖር በወንድየው እና በሴቲቱ የስጋ ዘመዶች መካከል እንዲሁም በሴትየዋና በወንድየው የስጋ ዘመዶች መካከል አንዳችም የጋብቻ ዝምድናን አያስከትልም፡፡
2. ሆኖም የጋብቻ ዝምድና ባለ ጊዜ ጋብቻን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች ጋብቻ ሣይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ባለ ግዜም ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 112 የጋራ ኑሮ ወጪዎችን ስለመሸፈን**

ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች የጋራ ኑሮአቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 113 ስለ ጋራ ሀብት**

1. የንብረት አስተዳደራቸውን አስመልክቶ የሚያደርጉት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ከሶስት አመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነቱ ውስጥ ያሉ ያፈሯቸው ንብረቶች የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ፡፡
2. ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ አብረው በመኖር ላይ እያሉ የሚኖሯቸው ንብረቶች በግንኙነቱ ውስጥ የተፈሩ ሀብቶች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡
3. ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት የሚገቧቸው እዳዎች አብርው በሚኖሩበት ጊዜ ለጋራ ኑሮአቸው ወይም ከግንኙነቱ የተወለዱ ልጆቻቸውን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል የተገቡ እዳዎች ሲሆኑ ለእዳዎቹ አከፋፈል ሁለቱም በአንድነትና በነጠላ ሃላፊዎች ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 114 የጋራ ንብረት ስለሚያስከትለው ውጤት**

ከዚህ በላይ በንቀጽ 113 ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር በተመለከተው መሠረት የጋራ ሀብት በሚፈጠርበት ጊዜ ስለዚሁ ንብረት አስተደደር፣የሶስተኛ ወገኖች እዳ አከፋፈልና የንብረት ማጣራት ሂደት በዚህ ሕግ በጋብቻ ስለሚፈጠር የጋራ ንብረትና የማጣራቱ ሂደት አስቀድመው የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል /አንቀጽ 96-104/

**አንቀጽ 115 የልጆች መወለድ**

ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ ወንድና ሴት የተወለዱት ልጆች ተወላጅነታቸው የሚረጋገጠው በዚህ ሕግ ስለመወለድ በተፃፈው ምእራፍ ውስጥ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**አንቀጽ 116 የግንኙነቱ መቋረጥ**

1. ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት በማናቸውም ጊዜ ግንኙነታቸው እንዲቋረጥ ማድረግ ይችላሉ፡፡
2. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 113 ሥር ስለ ጋራ ሀብት የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ያደረገው ወገን ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ካሣ እንዲከፍል አይገደድም፡፡

**አንቀጽ 117 የግንኙነቱ ማስረጃ**

1. ጋብቻ ሣይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖርን የግንኙነቱ ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላል፡፡
2. አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው ይኖራሉ የሚባለው ምንም እንኳን በሕግ የተጋቡ ባይሆኑም የተጋቡ ስዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው ሲገምቷቸው ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተው ሁኔታ መኖሩን አንደኛው ወገን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደ ባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ናቸው ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል፡፡
4. ከዚህ በላይ የተመለከተውን የሕግ ግምት ማናቸውንም አይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ግንኙነቱ ያለመኖሩን በማስረዳት ማፍርስ ይቻላል፡፡

**አንቀጽ 118 ጋብቻ ሣይፈጸም የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች**

1. ከጋብቻ ሥርዓት ወይም ጋብቻ ሣይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ከመኖር ውጭ በአንድ ወንድ እና በአንዲት ሴት መካከል የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች በሕግ ፊት ምንም ውጤት አይኖራቸውም፡፡
2. በዚህ ሕግ ስለ ጉዲፈቻ ልጅ ወይም ልጅነትን ስለመቀበል የተወሰኑት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከእንደዚህ ያለው ግንኙነት የተወለዱ ልጆች ከእናታቸው በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር ማናቸውም አይነት ሕጋዊ ግንኙነት አይኖራቸውም፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የጋብቻ እና ጋብቻ ሣይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ በመኖር ረገድ የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**አንቀጽ 119 ተፈጻሚነት ስለሚኖረው ሕግ**

በዚህ ሕግ የተመለከቱት የስነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ሕግ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ለሚነሱ ክርክሮች በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ፍትሐብሄር ሥነሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ 120 የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት የተደነገጉት ተፈጻሚ ስለመሆናቸው**

1. ጋብቻው የፈረሰው በፍች ባይሆንም እንኳ የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት ከዚህ በላይ በምዕራፍ 6 ሥር የተፃፉት ድንጋጌዎች እንደየ አግባብነታቸው ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡
2. በተለይም ጋብቻው የፈረሰው በሞት በሆነ ጊዜ በህይወት ባለው ተጋቢ እና በሟች ወራሾች መካከል የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ክርክር የተነሣ እንደሆነ የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት ከዚህ በላይ በምዕራፍ 6 የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈጻሚዎች የሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 121 የባልና ሚስት ክርክር ስለሚታይበት ሁኔታ**

ፍርድ ቤት የባልና ሚስትን ክርክር በሚያይበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ ሆኖ ከአገኘው ባልና ሚስቱን በአንድነት ወይም በተናጠል በሚያነጋገርበት ጊዜ ወይም ጉዳዩን ሲመረምርና ምስክር ሲሰማ በዝግ ያስችላል፡፡

**አንቀጽ 122 ስለውሣኔ አሰጣጥ**

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ፍችን በሚወስንበት ጊዜ የተጋቢዎችን ወይም የቤተዘመዶቻቸውን መልካም ስም ለመጠበቅ ዝርዝር ጉዳዮችን ከመተቸት በመቆጠብ ፍችውን ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ብቻ በውሣኔው ላይ ሊያሰፍር ይችላል፡፡

**አንቀጽ 123 ስለ ይግባኝ**

ፍርድ ቤቱ ፍች መወሰኑን ብቻ መሠረት በማድረግ ይግባኝ መጠየቅ አይቻልም፡፡

**አንቀጽ 124 የልጆችን አጠባበቅና አያያዝ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ስለሚሰጠው ውሣኔ**

1. ፍርድ ቤቱ ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወስን ልጆች ከማን ጋር ሊኖሩ እንደሚገባ፣ስለትምህርታቸውና ስለጤናቸው አጠባበቅ፣ ስለቀለባቸውና ባጠቃላይም ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ወላጆችና ልጆቻቸው ለመጠያየቅ ስላላቸው መብት መወሰን አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ የወላጆችን የገቢ፣የእድሜ፣የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ፣እንዲሁም የልጆቹን እድሜ ፣ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማገናዘብ ይኖርበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ስር በሰፈሩት ድንጋጌዎች መሠረት የተለየ ውሳኔ እንዲሰጥ አስገዳጅ ምክንያት ካላጋጠመው በስተቀር ፍርድ ቤቱ አምስት ዓመት ያልሞላቸው ሕፃናት እስከዚሁ እድሜ ድረስ በእናታቸው እጅ እንዲቆዩ ማዘዝ አለበት፡፡
4. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ስለ ልጆች አያያዝና አጠባበቅ የሚሰጠው ውሣኔ የሁኔታዎችን መለዋወጥ ምክንያት በማድረግ በሚቀርብ ጥያቄ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 125 ጋብቻ ሣይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር**

በዚህ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ጋብቻ ሣይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎች ላይ ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ፍርድ ቤት ስልጣን

**አንቀጽ 126 የሚፀና ጋብቻ ስለመኖሩ**

ጋብቻ የተፈጸመ ወይም የሚፀና ስለመሆኑ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 127 ጋብቻ ሣይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖር**

በአንድ ወንድ እና በአንዲት ሴት መካከል ጋብቻ ሣይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ስለመኖሩ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 128 ስለ ፍችና ውጤቶቹ**

ፍችን የመወሰን ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 94 በተደነገገው መሠረት የፍች ውጤቶችን በተመለከተ ውሣኔ የመስጠት ወይም የማጽደቅ ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 129 በጋብቻ ውስጥ ስለሚፈጠሩ አለመግባባቶች**

1. ከዚህ በላይ ባለው አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ባልና ሚስቱ በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ይወሰናሉ፡፡
2. ሽማግሌዎቹ በሚሰጡት ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ሥልጣን ላለው የወረዳ ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በሽማግሌዎቹ የተሠጠው ውሣኔ ሊያፀና፣ሊያሻሽል ወይም ሊሽር ይችላል፤የሚሰጠውም ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ስለ እርቅ

**አንቀጽ 130 አስታራቂ ሽማግሌዎችን ስለመምረጥ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 93/2/ መሠረት ባልና ሚስት ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ በወሰኑ ጊዜ አመች ሆኖ በሚያገኙት መንገድ አንድ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሽማግሌዎችን በመምረጥ ሽማግሌ እንዲመርጡ ከተነገራቸው ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ የሽማግሌዎቹን ስም ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ ማሣወቅ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሽማግሌዎች ስም ዝርዝር ሲቀርብለት ወይም ሽማግሌዎቹ እንደቀረቡ ወዲያውኑ መዝግቦ እርቁ የሚከናወንበትን የመፍትሄ አቅጣጫ የሚጠቁም ምክርና መመሪያ በመስጠት ወይም እንዲደርሣቸው በማድረግ እርቅ ወይም የእርቁ ሙከራ ውጤት በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብለት ያዝዛል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /2/ ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የእርቁ ሂደት የደረሰበትን ደረጃ በየጊዜው ለመመርመርና ወቅታዊ ሪፖርት እንዲቀርብለት ማዘዝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 131 ስለተጨማሪ ጊዜ**

ከእርቅ ሙከራው ሂደት አኳያ ባልና ሚስት ያለመግባባታቸውን በእርቅ ሊጨርሱ ይችላሉ የሚል ግምት ያለው አንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 130/2/ሥር በተመለከተው ጊዜ ሣይገደብ ከአንድ ወር ያልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት የእርቅ ሙከራው እንዲቀጥል ሊያዝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 132 የአስታራቂ ሽማግሌዎች ኃላፊነት**

1. አስታራቂ ሽማግሌዎች ባልና ሚስቱ የመፋታት አሣባቸውን እንዲተውና ጉዳያቸውን በመግባባት እንዲጨርሱ ለማድረግ ያላሠለሰ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡
2. አስታራቂ ሽማግሌዎቹ ጉዳዩ ከፍች በመለሰ ሊፈታ እንደማይችል የተረዱ እንደሆነ ተጨማሪ ጊዜ ሣያስፈልጋቸው ስለደረሱበት ውጤት ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. አስታራቂ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ከፍች በመለስ በማግባባት ለመፍታት ከመጣር አልፈው ባልና ሚስቱን የሚመለከት ማናቸውንም ትእዛዝም ሆነ ውሣኔ የመስጠት ስልጣን አይኖራቸውም፡፡

**አንቀጽ 133 የሪፖርት አለመቅረብ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 130 እና 131 ድንጋጌዎች መሠረት አስታራቂ ሽማግሌዎች ሪፖርት ሣያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይዘጋዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው ጉዳያቸውን በእርቅ አለመጨረሳቸውንና ሪፖርቱ በወቅቱ ያልቀረበበትን ምክንያት በመግለጽ ጉዳያቸው እንዲንቀሳቀስላቸው የጠየቁ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥያቄአቸው ተገቢ ሆኖ ካገኘው መዝገቡን እንደገና በመክፈት በሕጉ መሠረት የራሱን ውሣኔ ይሰጣል፡፡
3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ/1/ መሠረት ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው መዝገቡን የመዝጋት ውሣኔ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው አዲስ አቤቱታ በማቅረብ ጉዳያቸው እንዲታይላቸው ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይሆንም፡፡

## ምዕራፍ አሥር

## ስለመወለድ

## ክፍል አንድ

## አባትነትንና እናትነትን ስለማወቅ

### ንዑስ ክፍል 1

### አጠቃላይ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 134 የሕጉ ድንጋጌዎች አስገዳጅ ስለመሆናቸው**

ሕጉ በግልጽ የሚፈቅድ ካልሆነ በስተቀር አባትነትንና እናትነትን ስለማወቅ የተፃፉት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በስምምነት ሊለወጡ አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 135 ስለ እናትነት**

እናት የተባለችው ሴት ልጁን የወለደችው እርሷ በመሆንዋ ብቻ እናትነትዋ ይታወቃል፡፡

**አንቀጽ 136 ስለ አባትነት**

1. ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በእናትየዋና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት ለመኖሩ በመረጋገጡ ምክንያት አባትነት ይታወቃል፡፡
2. አባትየው ልጁን ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ምክንያት አባትነት ሊታወቅ ይችላል፡፡
3. በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሣኔም  አባትነት እንዲታወቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

### ንዑስ ክፍል ሁለት

### አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅ ስለመሆኑ

**አንቀጽ 137 ባል አባት ነው ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ**

በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ነው፡፡

**አንቀጽ 138 የግምቱ አጠቃላይነት**

**1.** ከልጁ ጋር ያለው የእናት ግንኙነት በየትኛውም ዘዴ የተረጋገጠ ቢሆንም ከዚህ በላይ በአንቀጽ137 ሥር
የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡
2. የልጁ የልደት ምስክር ወረቀት ባልየው አባት ያለመሆኑን ወይም የልጁ አባት ሌላ ሰው መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም እንኳ ይኸው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የኖረዋል፡፡
3. ከዚህ በላይ የተመለከተው ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የልደት ምስክር ወረቀቱ እንዲታረም ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 139 እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ**

1. ጋብቻው ከተፈፀመ ከ180 ቀናት በኋላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል፡፡
2. ለዚህ ተቃራኒ የሆነ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 140 የባልየው መጥፋት**

በዚህ ሕግ ስለአባትነት የተደነገጉት የሕግ ግምቶች በሕግ አባት ነው የሚባለው ሰው መጥፋቱ በተነገረበት ፍርድ ላይ ስለመኖሩ ወሬ የተሰማበት የመጨረሻ ቀን ነው ከተባለበት ከ 300 ቀናት በኋላ ለተወለደው ልጅ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 141 ጋብቻ ሣይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር**

1. አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ በዚሁ ግንኙነት ከእናትየዋ ጋር አብሮ የሚኖረው ሰው ነው፡፡
2. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 138 እና 139 ሥር ስለግምቱ አጠቃላይነትና እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ የተመለከቱት  ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ሥር በተመለከተው የሕግ ግምትም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

### ንዑስ ክፍል ሶሶት

### ልጅነትን ስለመቀበል

**አንቀጽ 142**

**1. መሠረቱ**

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ሊታወቅ ያልቻለ እንደሆነ አባትየው ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ ምክንያት ሊታወቅ ይችላል፡፡

www.abyssinialaw.com

**አንቀጽ 143**

2. **ትርጓሜ**

አንድ ሰው አንድን የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ የእርሱ ልጅ መሆኑን አምኖ በመቀበል ቃሉን የሰጠ እንደሆነ የዚሁ ልጅ አባት መሆኑን ተቀበለ ይባላል፡፡

**አንቀጽ 144**

3. **ሥርዓት /ፎርም/**

አንድ ሰው በመግለጽ በሚሰጠው ቃል ወይም በጽሁፍ በሚያደርገው ኑዛዜ ወይም በሌላ በማናቸውም ስልጣን በተሰጠው አካል በተረጋገጠ ሰነድ አማካኝነት አባት መሆኑን በመግለጽ ልጅነትን ለመቀበል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 145 ስለ ወኪልነት**

1. አካለ መጠን ያልደረሰ ቢሆንም እንኳን ልጄ ነው ሲል ቃል ለመስጠት የሚችለው አባት ብቻ ነው፡፡
2. ቃሉን ሌላ ሰው እንዲሰጥለት ማድረግ የሚችለው ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው የፍትህ አካል የፀደቀ ልዩ የውክልና ስልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል፡፡
3. በፍርድ የተከለከለ ሰው ቃሉን በራሱ ወይም ፍርድ ቤት ሲፈቅድ በእርሱ ስም በሕጋዊ ወኪሉ አማካኝነት ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 146 የአባትየው መሞት**

የልጁ አባት የሞተ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል በሆነ ጊዜ ከአባትየው ወላጆች አንዱ በእርሱ ስም ልጁን ሊቀበል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 147 እናት የተቀባዩን አባትነት ስላለማመንዋ**

1. የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እውነትነት ያለው መሆኑን ካላመነች በስተቀር አባት ልጄ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል በሕግ ፊት ውጤት አይኖረውም፡፡
2. የልጁ እናት የሞተች ወይም ፈቃድዋን ለመግለጽ የማትችል ሆና የተገኘች እንደሆነ የእምነት ቃሉ ከልጁ እናት ወላጆች በአንደኛው ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. የልጁ እናት ወላጆች በሌሉ ጊዜ ወደላይ በሚቆጠር ሌላ ወላጅ ወይም በፍርድ በተከለከለው ሰው አሣዳሪ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 148 ስለ ልጁ ለአካለ መጠን መድረስ**

ልጅነትን የመቀበሉ ተግባር የተከናወነው ልጁ ራሱ አካለ መጠን ከደረሰ በኂላ የሆነ እንደሆነ አባት ልጁን መቀበሉ ውጤት የሚያገኘው ልጁ አባትነቱን የተቀበለ እንደሆነ ነው፡፡

**አንቀጽ 149 አምኖ የመቀበሉ ሁኔታ**

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 147 እና አንቀጽ 148 ሥር የተመለከቱት ሰዎች የመቀበሉ ድርጊት መከናወኑን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ክርክር ያላነሱ እንደሆነ አምነው እንደተቀበሉ ይቆጠራል፡፡

**አንቀጽ 150 የልጁ መሞት**

ልጅየው ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ተክቶ ካልሞተ በስተቀር ልጅነቱን አውቆ መቀበል አይችልም፡፡

**አንቀጽ 151 ቃልን ስለመሻር**

1. ልጄ ነው ሲል አባት የሰጠውን ቃል መሻር አይችልም፡፡
2. አሣዳሪው አስቀድሞ ስምምነቱን ካልሰጠ በስተቀር ልጅነትን የተቀበለ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አካለመጠን ከመድረሱ በፊትና አካለ መጠን ከደረሰም በኂላ እስከ አንድ አመት ጊዜ ድረስ ልጄ ነው ሲል የሰጠውን ቃል ሊሽር ይችላል፡፡
3. ልጄ ነው ሲል የተቀበለበትን ቃሉን ለመሻር ብቸኛ መብት ያለው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ብቻ ነው፡፡ የልጁ ሕጋዊ ወኪሎችም ሆኑ ወራሾቹ በዚህ መብት መጠቀም አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 152 ስለማፍረስ**

1. ልጅነትን ለመቀበል የተነገረ ቃል በኃይል የተሰጠ መሆኑን በማስርዳት ሊፈርስ ይችላል፡፡
2. ልጄ ነው ተብሎ ከተቀበለው ሰው ሊፀነስ የማይችል ለመሆኑ በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር ልጅነትን የመቀበሉ ድርጊት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ሊፈርስ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 153 አንድን ልጅ ብዙ አባቶች ሊቀበሉት ስላለመቻላቸው፡፡**

ቀደም ሲል የተሰጠ ልጅነትን የመቀበል ቃል እንዲፈርስ ካልተደረገ በስተቀር ሌላ ሰው ልጄ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**ንዑስ ክፍል አራት**

**በፍርድ ቤት ውሣኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ**

**አንቀጽ 154 - 1 በፍርድ ስለሚነገር አባትነት**

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ያልታወቀ ወይም የተካደ እንደሆነና ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ አባትነት በፍርድ ውሣኔ ሊታወቅ ይችላል፡-

ሀ. ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የመደፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር የተፈጸመባት ሲሆን፤

ለ. ሆን ተብሎ በተደረገ የተንኮል ድርጊት፣ስልጣንን ያለአግባባ በመጠቀም፣አገባሻለሁ ሲል የተስፋ ቃል በመስጠት ወይም በሌላ ተመሣሣይ መንገድ ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የማሳት ተግባር የተፈጸመባት ሲሆን፤

ሐ. አባት ነው በተባለው ሰው የተጻፋና በማያሻማ ሁኔታ አባትነቱን የሚያረጋግጡ ደብዳቤዎች ወይም ሌሎች ጽሁፎች ሲኖሩ፤

መ. በሕግ የታወቀ ግንኙነት ሣይኖራቸው የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረስጋ ግንኘነት አብረው የኖሩ እንደሆነ፤

ሠ. አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ፣በማስተማር ወይም በማሣደጉ ላይ እንደአባት በመሆን የተሣተፈ አንደሆነ፡፡

**<u>አንቀጽ 155 – 2 አባትነትን በፍርድ ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ክስ</u>**

ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን አባትነት በፍርድ እንዲነገር የሚቀርብ ክስ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ባሉ ጊዜ ተቀባይነት አይኖረውም፡-

ሀ. ሌላኛው ሰው የልጁ አባት ላለመሆኑ በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የህክምና ዘዴ ካልተረጋገጠ በስተቀር በሕግ በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸምዋ የተረጋገጠ እንደሆነ፤

ለ. አባት ነው የተባለው ሰው በሕግ በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ በመጥፋቱ ወይም በአደጋ ምክንያት አባት ሊሆን የማይችልበትን ሁኔታ ሲያረጋጋጥ፤

ሐ. አባት ነው የተባለው ሰው በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የህክምና ዘዴ የልጁ አባት ሊሆን የማይችል መሆኑን ሲያረጋግጥ፡፡

**<u>አንቀጽ 156 ሌላ ሁኔታ ስላለመኖሩ</u>**

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 154 ሥር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ አባትነት በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊታወቅ አይችልም፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>አባትነትን በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የሕግ ግጭት</u>**

**<u>አንቀጽ 157 አባትንትን ስለመወሰን</u>**

1. **<u>*መሠረቱ*</u>**

ከዚህ በላይ የተመለቱትን አንቀጾች ተፈጻሚ በማድረግ አንድ ልጅ ከአንድ በላይ አባቶች አሉት ከተባለ የልጁ አባትነት በሕግ በሚሰጣቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት ሊወሰን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 158 – 2 ሥርዓት/ፎርም/</u>**

1. የአባትነት ውሣኔ የሚያሰጠውን ስምምነት ሶሶት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው ይገባል፡፡
2. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የልጁን እናት ቃል መስማት ይገባል፡፡

**<u>አንቀጽ 159 የሕግ ግምት</u>**

ስለ አባትነት በሚደረገው ክርክር ስምምነት ያልተገኘ እንደሆነና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ሁለት የሕግ ግምቶች በመከተል ይፈጸማል፡-

ሀ. ጋብቻ ሣይፈጸም እንደ ባል ከሚኖር ሰው ይልቅ ህጋዊው ባል ይመረጣል፤

ለ. ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ከነበረው ባል ወይም ከሴትየዋ ጋር አብሮ ይኖር ከነበረው ሰው ይልቅ እናቲቱ ልጁን ስትወልድ የነበራት ባል ወይም አብሯት የሚኖር ሰው የልጁ አባት ነው ማለት ይገባል፡፡

**<u>አንቀጽ 160 – 1 አባትነትን በስምምነት ስለማስተላለፍ</u>**

1. ልጁ ተወለደው ጋብቻው ከተፈጸመ ወይም ጋብቻ ሣይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖሩ ከተጀመረ አንስቶ በ210 ቀናት ውስጥ የሆነ እንደሆነ ባልየው ወይም ከሴትየዋ ጋር እንደባል አብሮ የሚኖረው ሰው የልጁ አባት እኔ ነኝ ለሚል ሌላ ሰው በስምምነት አባትነቱን ሊያስተላልፍለት ይችላል፡፡
2. እንዲሁም ልጁ ከጋብቻው መፍረስ ወይም እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖሩ ከተቋረጠበት ቀን በኂላ 210 ቀኖችን አሣልፎ ተወልዶ እንደሆነ ባልየው ወይም እንደ ባል አብሮ የኖረው ሰው ከዚህ በላይ የተነገረው መብት ይኖረዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 161 – 2 ሥርዓት /ፎርም/</u>**

1. በስምምነት የሚደረግ አባትነትን የማስተላለፍ ድርጊት ሶስት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሠጠው የፍትህ አካል ሊያፀድቀው ይገባል፡፡
2. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የእናቲቱ ቃል መስማት አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 162 ስለ ወኪልነት</u>**

1. በዚህ ክፍል ውስጥ የተመለከቱትን ስምምነቶች አካለ መጠን የደረሱና በፍርድ ያልተከለከሉ ባለጉዳዮች ራሣቸው መጨረስ አለባቸው፡፡
2. ማናቸውም ባለጉዳይ ስምምነቱን ሌላ ሰው እንዲያከናውንለት ማድረግ የሚችለው በፍርድ ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሠጠው የፍትህ አካል የፀደቀ ልዩ የውክልና ስልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**አንቀጽ 163 ቃልን ስለመሻር**

አባትነትን በስምምነት የመወሰ ን ወይም የማስተላለፍ ድርጊት ሊሻር አይችልም፡፡

**አንቀጽ 164 ስለማፍረስ**

1. ልጅነትን ለመቀበል የተደረገ ስምምነት በሀይል ድርጊት የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል፡፡
2. ልጄ ነው ብሎ ከተቀበለው ሰው ሊፀነስ የማይችል ለመሆኑ በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር ልጅነትን የመቀበሉ ስምምነት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ሊፈርስ አይችልም፡፡

**ክፍል ሶስት**

**ስለ ልጅነት ማስረጃ**

**አንቀጽ 165 የልደት ምስክር ወረቀት**

በአባትነት ወይም በእናትነት በኩል የአንድ ሰው ልጅነት የእገሌ ልጅ ነው የሚል የልደት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ይረጋገጣል፡፡

**አንቀጽ 166 የልደት ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ**

የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማሣየት ልጅነት ይረጋገጣል፡፡

**አንቀጽ 167 የልጅነት ሁኔታ መኖር 1. ትርጓሜ**

አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው የማህበረሰቡ ዘንድ የእሱ ወይም የእሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን ነው፡፡

**አንቀጽ 168 – 2 ልጅነትን በልጅነት ሁኔታ ስለማስረዳት**

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ልጁ ነው ሲል የህግ ግምት ይወስዳል፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ/1/ ሥር የተመለከተውን ግምት ልጁ ነው የተባለው ሰው በእርግጥ ልጅ ሊሆን እንደማይችል በማስረዳት ማፍረስ ይቻላል፡፡

**አንቀጽ 169 ተወላጅነትን ለማስረዳት ስለሚቀርብ ክስ**

1. የልጅነት ሁኔታ የሌለ እንደሆነ ተወላጅነትን በምስክሮች ወይም ማናቸውም አይነት ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል፡፡
2. ተወላጅነትን የማረጋገጥ ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም፡፡
3. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉት ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 170 ክስን ስላለመቀበል**

ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ የሚፈልገው ሰው ስለመወለዱ ከተሰጠው የልደት ምስክር ወረቀት ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ ከሌላ ሰው ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ አይፈቀድለትም፡፡

**አንቀጽ 171 ስለ ከሣሽ**

1. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ የሚችሉት ልጁ ወይም አሣዳሪው ወይም ወራሾቹ ናቸው፡፡
2. እንደዚሁም የልጁ አባት ወይም እናት ነን የሚሉት ሰዎች ክስ ለማቅረብ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 172 ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ**

1. ልጁ በህይወት እስካለ ድረስ ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. የልጁ ወላጆች ወይም አሣዳሪዎች ልጁ አካለመጠን ባልደረሰበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ክስ ለማቅረብ አይችሉም፡፡
3. ልጁ ሀያ አመት ሣይሞላው የሞተ እንደሆነ እርሱ፣ከሞተ በኃላ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ወራሾቹ ክስ ለማቅረብ አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 173 ስለተከሣሽ**

1. ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክሱን ያቀረበችው እናት ነኝ የምትል ሴት በሆነች ጊዜ ክሱ የሚቀርበው በልጁ ላይ ነው፡፡
2. ሆኖም ክሱ የቀረበው በሌላ ሰው ሲሆን ክሱ የሚቀርበው እናት ነች በተባለችው ወይም በወራሾችዋ ላይ ነው፡፡

**ክፍል አራት**

**በተወላጅነት ላይ ስለሚነሣ ክርክር ፣ስለ መካድ**

**ንኡስ ክፍል አንድ**

**በተወላጅነት ላይ ስለሚነሣ ክርክር**

**አንቀጽ 174 መሠረቱ**

በእናት በኩል ያለው ተወላጅነት በማንኛውም ባለጉዳይ በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ክርክር ሊደረግበት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 175 ክስን ስለመቀበል**

1. በተወላጅነት ላይ ስለሚደረገው ክርክር የሚቀርበው ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም፡፡
2. በተወላጅነት ላይ ክርክር ለማድረግ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉትን ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

**አንቀጽ 176 ክስን ስላለመቀበል**

ልጁ ተወላጅነቱን የሚያረጋግጥ የልደት ምስክር ወቀትና ከዚህ ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ በተወላጅነቱ ላይ ለመከራከር ፈቃድ አይሰጥም፡፡

**አንቀጽ 177 ስለ ተከሣሽ**

1. በተወላጅነት ምክንያት የሚቀርበው ክስ በተወላጅነቱ ላይ ክርክር በተነሣበት ሰው ላይ ወይም በወራሾቹ ላይ ይመሠረታል፡፡
2. የልጁን እናት ተገቢ ሆኖ ሲገኝም የልጁን አባት ክርክሩ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**ስለመካድ**

**አንቀጽ 178 መሠረቱ**

በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 179 ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ስላለመኖሩ**

**1. መሠረቱ**

የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በ 300ኛውና 180ኛው ቀናት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ላለመፈጸሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስረዳ እንደሆነ የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 180 – 2 የሕግ ግምት**

1. ከሁለቱ አንደኛው ባቀረበው የመፋታት ጥያቄ መሠረት ወይም በሁለቱ መካከል በተደረገው የመለያየት ስምምነት ምክንያት ባልና ሚስቱ በእውነት ተለያይተው በነበሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሩካቤ ስጋ ግንኙነት እንዳልተደረገ ይገመታል፡፡
2. ለዚህ ተቃራኒ ሆኖ የሚቀርበው ማስረጃ በማናቸውም ምክንያቶች ቢሆን ይሰማል፡፡

**አንቀጽ 181 አባት ለመሆን ስለአለመቻሉ 1. መሠረቱ**

በሕግ የልጁ አባት ነህ የተባለው ሰው የዚሁ ልጅ አባት ሊሆን በጭራሽ አለመቻሉን በማያጠራጥር አኳኋን በማስረዳት ለመካድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 182 – 2 ክስን ለመቀበል ስለመቻል**

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የሚቀርበው የመካድ ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም፡፡
2. ፈቃዱም የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርገው በቂና አስተማማኝ ከሆነ መረጃ የሚመነጭ የህሊና ግምት ወይም ከባድ ምልክት ሲኖር ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 183 – 3 ስለ ህሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች**

1. የህሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች የሚባሉት ልጅህ ነው ከተባለው ሰው አባትነት ጋር የማይስማሙ ለመሆናቸው በሣይንሳዊ እውቀት ተለይተው የሚታዩ ተጨባጭ መረጃዎች ሊሆኑ የችላሉ፡፡
2. እንዲሁም እነዚህ ነገሮች ሴቲቱ በሰውየው አባትነት ላይ ጥርጣሬ በሚያሣድር አኳኋን የልጁን መወለድ ወይም እርግዝናዋን ከሰውየው ከደበቀችበት ድርጊት ሊመነጩ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 184 – 4 ስለ ሴሰኝነት /በባል ላይ ስለሚደረግ ዝሙት/ ወይም ስለ እናቲቱ ማመን**

እናቲቱ በባልዋ ላይ ያደረገችው የሴሰኝነት /የዝሙት/ ሥራ ወይም ልጁ የሌላ ሰው ለመሆኑ የምትሰጠው የእምነት ቃል ብቻ እንደ ከባድ ምክንያቶች ወይም ምልክቶች ሊቆጠሩ አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 185 ስለ ከሣሽ**

1. የእኔ ልጅ አይደለም ብሎ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችለው የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ ግምት የሚሰጠው ሰው ብቻ ነው፡፡
2. በዚህ ጉዳይ በተለይ እናቲቱ፣አባት ነኝ ባዩ፣ አቃቤ ህግ ወይም ልጁ ራሱ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 186 በፍርድ የተከለከለ ሰው**

1. በፍርድ የተከለከለ ማናቸውም ሰው ፍርድ ቤትን አስፈቅዶ የመካድ ክስ ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. እንዲሁም በፍርድ የተከለከለው ሰው አሣዳሪ ይህንኑ የፍርድ ቤት ፈቃድ ከተቀበለ በኂላ በፍርድ በተከለከለው ሰው ስም ሆኖ የመካድ ክስ ለማቅረብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 187 ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ 1. መሠረቱ**

1. የእኔ ልጅ አይደለም የሚል የመካድ ክስ ከሳሹ የልጁን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ በ 180 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
2. እናትነት የተወሰነው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ በቀረበ ክስ ሲሆን የመካድ ክስ የሚቀርበው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ የቀረበውን ክስ የሚወስን የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 180 ቀናት ውስጥ ነው፡፡

**አንቀጽ 188 – 2 ልዩ ሁኔታ**

1. በህግ ግምት የልጁ አባት ነህ የሚባለው ሰው የሞተ ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ የተወሰነው ጊዜ ውስጥ ችሎታውን ያጣ እንደሆነ ከተወላጆቹ አንዱ በርሱ ፋንታ ሆኖ የመካድ ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. ተወላጆቹ የሌሉ እንደሆነ አባትና እናቱ፣እነዚህም የሌሉ እንደሆነ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ አንዱ መብቱን ሊሠራበት ይችላል፡፡
3. ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች የሌሉት እንደሆነ የተባለውን መብት ማናቸውም ሌላ ሰው/ወራሽን ወይም ወኪልን ሣይጨምር/ ከወንድሞቹ ወይም ከእህቶቹ አንዱ ሊሠራበት ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 189 ክስን ስላለመቀበል</u>**

ባልየው በጽሁፍ በሰጠው ፈቃድ መሠረት ልጁ በሰው ሠራሽ ዘዴ የተፀነሰ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡

**<u>አንቀጽ 190 ስለተከሣሾች</u>**

1. የመካድ ክስ በልጁ ላይ፣እርሱም ሞቶ እንደሆነ በወራሾቹ ላይ ይቀርባል፡፡
2. የልጁን እናት በሚቀርበው ክስ ውስጥ እንድትገባ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
3. ልጁ አካለመጠን ያልደረሰ ከሆነ ፍርድ ቤት በተለይ ለዚህ ጉዳይ የመረጠው ሞግዚት ወኪል ይሆነዋል፡፡

**<u>ምዕራፍ አሥራ አንድ</u>**

**<u>ስለጉዲፈቻ</u>**

**<u>አንቀጽ 191 ስለ ጉዲፈቻ ዝምጽና 1. መሠረቱ</u>**

በአንድ ሰውና በአንድ ልጅ መካከል በሚደረግ ስምምነት የጉዲፈቻ ዝምድና ሊፈጠር ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 192 – 2 ውጤቱ</u>**

ከዚህ በታች በአንቀጽ 193 ሥር የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደ ጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ይቆጠራል፡፡

**<u>አንቀጽ 193 – 3 ልዩ ሁኔታ</u>**

1. ጉዲፈቻ የጉዲፍቻውን ስምምነት በግልጽ የተቃወሙትን ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደጐን የሚቆጠሩ ዘመዶች በሚመለከት ውጤት አይኖረውም፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ተቃውሞ ስምምነቱ ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው የፍትህ አካል መጽደቁ በታወቀ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በፍርድ ቤት መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር አይፀናም፡፡

**<u>አንቀጽ 194 የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት</u>**

1. የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት እንደተጠቀ ይቆያል፡፡
2. የጉዲፈቻ ልጅየው ሚስት /ባልና ተወላጆችም ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር የዝምድና ግንኙነት ይኖራቸዋል፡፡
3. በቀደምት ቤተሰቦቹና በጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ መካከል መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ለጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ 195 የጉዲፈቻ አድራጊው እድሜ</u>**

1. እድሜው ከ25 አመት ያላነሰ እና ከ65 አመት ያልበለጠ ማንኛውም ሰው የጉዲፈቻ አድራጊ ሊሆን ይችላል፡፡
2. ጉዲፈቻ አድራጊዎች ባልና ሚስት በሆኑ ጊዜ የአንዳቸው እድሜ 25 አመት የሞላ ከሆነ በቂ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 196 የጉዲፈቻው ልጅ እድሜ</u>**

እድሜው ከአሥራ ስምንት አመት በታች የሆነና ከሞግዚት አስተዳደ ነፃ ያልወጣ ማናቸውም ሰው የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 197 ያገባ ሰው ስለሚያደርገው የጉዲፈቻ ስምምነት</u>**

1. የጉዲፈቻ አድራጊው ያገባ በሚሆንበት ጊዜ ባልና ሚስቱ በጋራ ልጁን የጉዲፈቻ ልጃቸው የሚያደርጉት ካልሆነ በስተቀር የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ አይቻልም፡፡
2. የጉዲፈቻው ልጅ የጉዲፈቻ አድራጊው ባል ወይም ሚስት ልጅ በሆነ ጊዜ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ/1/ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
3. እንዲሁም ከባልና ከሚስት አንደኛው ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ሲሆን ተፈጻሚነት እይኖረውም፡፡

**<u>አንቀጽ 198 የተፀነሰን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ስለማድረግ</u>**

1. የተፀነሰን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ማድረግ ይቻላል፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ልጁ በተወለደ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ስምምነቱን በገዛ ፈቃድዋ ብቻ ለመሠረዝ ትችላለች፡፡

**<u>አንቀጽ 199 ስለ ጉዲፈቻ አድራጊው ልጆች</u>**

1. የጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ የጉዲፈቻ ስምምነት ከማድረግ የሚያግደው አይሆንም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሠጠው የፍትህ አካል የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ አስቀድሞ ጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ በጉዲፈቻ ልጁ መልካም አስተዳደግና ጥቅም ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 200 አንድ ልጅ ከአንድ በላይ ጉዲፈቻ አድራጊ ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ</u>**

www.abyssinialaw.com

1. ባልና ሚስት ካልሆኑ በስተቀር ማንኛውም ልጅ ለብዙ ሰዎች የጉዲፈቻ ልጅ ሊሆን አይችልም፡፡
2. ጉዲፈቻ አድራጊው የሞተ እንደሆነ ግን አዲስ የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ ይቻላል፡፡
3. ልጅየው የባልና ሚስት የጉዲፈቻ ልጅ ከሆነና ከባልና ከሚስቱ አንደኛው የሞተ እንደሆነ በህይወት ካለው ሰው ጋር የሚጋባው አዲስ ተጋቢ የጉዲፈቻ ልጅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

<u>**አንቀጽ 201 ስምምነቱን ስለሚያደርጉ ወገኖች**</u>

የጉዲፈቻው ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሣዳሪ መካከል ይደረጋል፡፡

<u>**አንቀጽ 202 የጉዲፈቻው ልጅ ወላጆች ፈቃድ**</u>

1. የልጁ አባትና እናት በህይወት ያሉና የታወቁ ከሆነ ልጁ የጉዲፈቻ ልጅ ይሆን ዘንድ ፈቃዳቸውን እንዲሰጡ ያስፈልጋል፡፡
2. ከወላጆቹ አንደኛው የሞተ፣የጠፋ ወይም የማይታወቅ አንደሆነ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ሲሆን ሌላኛው ወላጅ ፈቃዱን ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ከወላጆቹ አንዱ ፈቃዱን ለመስጠት ያልፈለገ እንደሆነና የልጁ እድሜ 10 አመትና ከዚያ በላይ ከሆነ ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው የፍትህ አካል የአንደኛውን ወላጅ ፈቃድና የልጁን አስተያየት በመጠየቅ ጉዲፈቻውን ሊያፀድቀው ይችላል፡፡
4. ልጁ ፈቃዱን ለመስጠት የሚችል ወደላይ የሚቆጠር ወላጅ የሌለው እንደሆነ ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው የፍትህ አካል ለልጁ ያለውን ጠቃሚነት ግምት ውስጥ በማስገባት የጉዲፈቻ ስምምነቱን ተቀብሎ ሊያፀድቀው ይችላል፡፡

<u>**አንቀጽ 203 ስለ መንግሥት ወይም የግል እጓለማውታን አሣዳጊ ተቋሞች**</u>

1. የመንግሥት ወይም የግል እጓለማውታን አሣዳጊ ተቋማት እያሣደጉት ያሉትን ማናቸውንም ልጅ ለጉዲፈቻ አድራጊዎች በስምምነት ለመስጠት ይችላሉ፡፡
2. ከዚህ በላይ የጠቀሱት ተቋማት አንድን ልጅ በስምምነት ከመስጠታቸው በፊት የህፃናትን ደህንነት ለመከታተል ስልጣን ለተሰጠው የመንግሥት አካል ስለልጁ ማንነት፣በምን ሁኔታ ተቋሙ እንደተረከበውና ስለጉዲፈቻ አድራጊው ግላዊ፣ማህበራዊና ኢክኖሚያዊ አቋም መግለጫ ማቅረብ አለባቸው፡፡

<u>**አንቀጽ 204 የጉዲፈቻ አድራጊው መደበኛ ስፍራ ከክልሉ ውጭ ሲሆን**</u>

1. የጉዲፈቻ አድራጊው መደበኛ ስፍራ ከክልሉ ውጭ ሲሆን ወይም የጉዲፈቻ አድራጊው እራሱ የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን እንደነገሩ ሁኔታ የህፃናትን ደህንነት ለመከታተል ስልጣን የተሰጠው የክልልም ሆነ የፌዴራል መንግሥት አካል ስለጉዲፈቻ አድራጊው ግላዊ፣ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አቋም አግባብ ያላቸውን መረጃዎች በማጠናቀርና በመመርመር ስምምነቱ ቢደረግ ለልጁ ጠቃሚነት ይኖረዋል ሲል አስተያየቱን ካልሰጠ በስተቀር የጉዲፈቻውን ስምምነት ፍርድ ቤት ተቀብሎ ሊያፀድቀው አይችልም፡፡
2. ከዚህ በላይ /በንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የተመለከተው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ ስምምነቱ ለልጁ ጠቃሚነት አይኖረውም ሲል የገመተ እንደሆነ የባለስልጣኑን አስተያየት ባለመቀበል ስምምነቱን ላያፀድቀው ይችላል፡፡
3. ፍርድ ቤቱም ከባለስልጣኑ የቀረበለት መረጃ በቂ መስሎ ያልታየው እንደሆነ አዲስ ምርመራ በማከናወን ተጨማሪ መረጃ እንዲቀርብለት ባለስልጣኑን ለማዘዝ፣እንዲሁም ሌሎች ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊ መስሎ የሚታያቸውንና በእጃቸው የሚገኘውን መረጃ እንዲያቀርቡ ወይም እንደአስፈላጊነቱ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ለማዘዝ ይችላል፡፡

<u>**አንቀጽ 205 የፍርድ ቤት ስልጣን**</u>

1. የጉዲፈቻ ስምምነት ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተጠቀሰው ፍርድ ቤት የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ አስቀድሞ በወሣኝ መልኩ ለልጁ መልካም አስተዳደግና ጥቅም የሚበጅ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 203 እና 204 ሥር የተመለከቱትን የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ በፊት የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡-

ሀ. ልጅየው ስለ ጉዲፈቻ ስምምነቱ ያለውን አስተያየት፣

ለ. አስቀድሞ ፈቃዱን ያልሰጠ ከሆነም የአሣዳሪውን አስተያየት፣

ሐ. ጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን ለማሣደግና ለመንከባከብ ያለውን ብቃት፣

መ. የጉዲፈቻ አድራጊው መደበኛ ስፍራ ከክልሉ ውጭ ሲሆን ወይም ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን ልጅየው እንደ ሁኔታው በክልሉ ወይም በሀገር ውስጥ የሚያድግበት እድልና ሁኔታ አለመኖሩ፣

ሠ. ጉዲፈቻ አድራጊው እንደ ልጁ አድርጎ እንደሚያሣድገውና አላግባብ መጠቀሚያ እንደማያደርገው ለመገመት የሚያስችል መረጃ መኖሩን፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ቁጥር ሠ ሥር የተመለከተውን በሚያጣራበት ጊዜ የጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

<u>**አንቀጽ 206 የጉዲፈቻ ስምምነት የማይሰረዝ ስለመሆኑ**</u>

www.abyssinialaw.com

1. የጉዲፈቻ ስምምነት ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ/2/ ከተመለከተው ሁኔታ ውጪ ሊሰረዝ አይችልም፡፡
2. ጉዲፈቻ አድራጊው በጉዲፈቻ የተቀበለውን ልጅ እንደ ልጁ በማሣደግ ፋንታ በባርነት ወይም ባርነትን በሚመስል ሁኔታ ወይም ከግብረገብ ውጪ በሆኑ ተግባሮች እንዲሠማራ በማድረግ መጠቀሚያ ያደረገው እንደሆነ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጐዳ አኳኋን የያዘው መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለመሠረዝ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 207 የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንዲሠረዝ አቤቱታ ስለማቅረብ</u>**

1. የጉዲፈቻው ልጅ ራሱ፣የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ስልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል ወይም በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ከዚህ በላይ በተመለተው አንቀጽ የተደነገገውን መሠረት በማድረግ የጉዲፈቻው ስምምነት እንዲሠረዝ አቤቱታ ለማቅርብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት አቤቱታ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ጉዲፈቻ አድራጊውን ከማስቀረቡ በፊት ለአቤቱታው ምክንያት ናቸው የተባሉት መረጃዎች እውነት ሆነው ቢገኙ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለማፍረስ በቂ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

**<u>ምዕራፍ አስራ ሁለት</u>**

**<u>ቀለብ የመስጠት ግዴታ</u>**

**<u>አንቀጽ 208 ስለ ግዴታው ይዘት</u>**

ከዚህ በታች በአንቀጽ 209 ድንጋጌዎች መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው እንደ ባለጉዳዮቹ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልማድ የሚስማማውን በመከተል ለቀለብ ተቀባዩ ምግብ፣መኖሪያ፣ልብስ፣ጤናውን የሚጠብቅበትንና እንደሁኔታው ለትምህርቱ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች መስጠት አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 209 ግዴታው በእነማን መካከል ያለ ስለመሆኑ</u>**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚኖረው በቀጥታ ወላጆችና ተወላጆች ወይም በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ነው፡፡
2. እንዲሁም በወንድማማቾችና በእህትማማቾች መካከልም ቀለብ የመስጠት ግዴታ ይኖራል፡፡

**<u>አንቀጽ 210 ግዴታው ስለሚቀርበት ሁኔታ</u>**

ጋብቻው የፈረሰው በሞት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ያለው ቀለብ የመስጠት ግዴታ ቀሪ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 211 ቀለብ ተቀባዩ መብቱን ስለሚያጣበት ሁኔታ</u>**

ቀለብ ተቀባዩ በቀለብ ሰጪው ወይም በዚሁ ሰው ወደላይና ወደታች በሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ተወላጆች ወይም ባል ወይም ሚስት ህይወት ወይም ንብረት ላይ የወንጀል ተግባር የፈጸመ ወይም ለመፈጸም የሞከረ እንደሆነ ቀለብ የመቀበል መብቱን ያጣል፡፡

**<u>አንቀጽ 212 ግዴታው እንዲኖር የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች</u>**

ቀለብ የመስጠት ግዴታ ተፈጻሚ የሚሆነው ቀለብ ጠያቂው ሠርቶ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነ ገቢ ለማግኘት አቅም የሌለውና በችግር ላይ የወደቀ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 213 ስለግዴታው አፈጻጸም</u>**

1. በመሠረቱ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚፈጸመው ቀለብ ሰጪው ለቀለብ ተቀባዩ የቀለቡን ገንዘብ በመስጠት ነው፡፡
2. የቀለቡ መጠን የሚወሰነው ቀለብ ጠያቂው ያለበትን ችግር እና የቀለብ ሰጪውን አቅም በማመዛዘን ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 214 ሁኔታውን ማሻሻል የሚቻል ስለመሆኑ</u>**

ቀለብ ሰጭው ወይም ተቀባዩ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ስለቀለቡ መጠን ወይም ስለቀለብ ተቀባዩ መኖሪያ የተሰጠውን ውሣኔ በማናቸውም ግዜ ማሻሻል ይቻላል፡፡

**<u>አንቀጽ 215 ቀለቡ ስለሚከፈልበት ቦታ</u>**

ቀለቡ የሚከፈለው በተቻለ መጠን ለቀለብ ተቀባዩ በሚያመቸው ቦታ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 216 የቀለብ ገንዘብ ሊተላለፍና ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ</u>**

1. ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ ሊተላለፍ ወይም ሊያዝ አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የተደነገገው ቢኖርም ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ የሚከፈልበት ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ቢሆንም እንኳ ቀለብ ተቀባዩ ላለበት ችግር እሣቢ ለሚሆኑ ለእርዳታ ለተቋቋሙ ድርጅቶች ሊተላለፍ ይችላል፡፡
3. እንዲሁም ለቀለብ ተቀባዩ ኑሮ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ያበደሩ ሌሎች ሰዎችን በተመለከተ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንጽ /1/ ድንጋጌ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**<u>አንቀጽ 217 – 2 የቀለብ ገንዘብ የማይጠራቀም ስለመሆኑ</u>**

www.abyssinialaw.com

ቀለብ ተቀባዩ ለኑሮው አስፈላጊ መሆኑን ካላረጋገጠ በስተቀር የቀለቡን ገንዘብ መቀበል ካለበት ቀን ጀምሮ በተከታዬቹ ሶስት ወራት ውስጥ ያልተቀበለው ወይም ሣይጠይቀው የቀረ እንደሆነ የተጠራቀመው ቀለብ እንዲሰጠው መጠየቅ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 218 ቀለብ ተቀባዩን በቀለብ ሰጭው ቤት ማኖር ስለመቻሉ**

1. ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ ተቀብሎ በማስቀመጥ ቀለብ የመስጠት ግዴታውን ሊፈጽም ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር ስለተመለተው ጉዳይ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የነገሩን አካባቢ ሁኔታዎች በመመልከት ተገቢ መስሎ የታየውን ይወስናል፡፡
3. ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ እንዲያስቀምጥ ምን ጊዜም ቢሆን አይገደድም፡፡

**አንቀጽ 219 ስለ ቀለብ ሰጭዎች ብዛት 1. መሠረቱ**

ለቀለብ ተቀባዩ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ የሆኑ እንደሆነ ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡን እንዲሰጠው ሊጠይቀው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 220 – 2 ስለ አቤቱታ**

1. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ ሆነው ከእነርሱ መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት ቀለቡን የከፈሉ እንደሆነ ሣይከፍሉ የቀሩት ወገኖች ድርሻቸውን እንዲከፍሏቸው ለመጠየቅ ይችላሉ፡፡

2 ከዚህ በላይ ባለው ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር ስለተመለከተው ጉዳይ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሣሾቹ ያላቸውን ሀብትና ከከሣሽ ጋር ያላቸውን የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ደረጃ በማመዛዘን ተከሣሾቹ የቀለቡን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍሉ ሊወስንባቸው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 221 – 3 ለቀለብ ሰጪዎች ስለሚሰጥ የከፋይነት ተራ**

በዚህ ሕግ አንቀጽ 209 መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸወ ሰዎች ቅደም ተከተል፡-

ሀ. በመጀመሪያ ደረጃ ባል ወይም ሚስት፣

ለ. በሁለተኛ ደረጃ ተወላጆች እንደየደረጃቸው፣

ሐ. በሶስተኛ ደረጃ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው፣

መ. በአራተኛ ደረጃ ወንድማማችና እህትማማቾች፣

ሠ. በአምስተኛ ደረጃ የጋብቻ ተወላጆች እንደየደረጃቸው፣

ረ. በስድስተኛ ደረጃ የጋብቻ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው፡፡

**አንቀጽ 222 በጋራ ቀለብ ሰጪዎች መካከል የሚደግ ስምምነት**

1. የጋራ ቀለብ ስጪዎች እርስ በርሣቸው ስለአላቸው ግንኙነት ለጋራ ቀለብ ተቀባያቸው ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡን እንዲሰጠው በማለት የሚፀና ስምምነት ለማድረግ ይችላል፡፡
2. ቀለብ ተቀባዩ ስምምነቱን ወዶ የተቀበለው እንደሆነ ይህንኑ ስምምነት የማያከብርበት ከባድ ምክንያት ካልተገኘ በስተቀር ቀለቡን ለመቀበል ሌሎችን ቀለብ ሰጪዎች መጠየቅ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 223 ስለ ጉዲፈቻ ልጅ ልዩ ሁኔታ**

1. የጉዲፈቻ ልጁ ባል ወይም ሚስትና የቀጥታ መስመር ተወላጆች የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተዘዶች ቀለቡን መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ካልተገኙ በስተቀር የሥር ወላጆቹን ቤተዘመዶች ቀለብ ለመጠየቅ አይችልም፡፡
2. የቀደምት ቤተሰቦቹ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ቀለብ ለማግኘት ከዘመዳቸው አንዱን ለመጠየቅ የማይችሉ ካልሆነ በስተቀር በጉዲፈቻ የሰጡትን ልጅ ቀለብ ሊጠይቁት አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 224 ስለ ሥርዐተ-ቀብር ወጭ**

1. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ለዚህ ለተባለው ሰው ሥርዓተ ቀብር የወጣውን ወጪ ለመክፈል ይገደዳል፡፡
2. ይህንኑ ወጪ ያደረገው ሰው ወጪውን እንዲተካለት ቀለብ ሰጪውን ለመጠየቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 225 ልዩ ስምምነቶች**

ልዩ ስምምነቶችን በማድረግ በዚህ ምእራፍ የተጻፉትን ድንጋጌዎች ለመለወጥ አይፈቀድም፡፡

## ምዕራፍ አስራ ሶሶት
## አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች
## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 226 ትርጓሜ**

አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሣይለይ ዕድሜው አሥራ ስምንት አመት ያልሞላው ልጅ ነው፡፡

**አንቀጽ 227 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የሌለው ስለመሆኑ**

1.አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ስለ መልካም አስተዳደጉና ደህንነቱ ጉዳይ በአንድ አሣዳሪው እየተጠበቀ ይቆያል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. ንብረት ነክ ጥቅሞቹንና በአጠቃላይ የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት በሞግዚቱ ይወከላል፡፡
3. በሕግ በግልጽ ለተመለከቱት ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ሕጋዊ ድርጊቶችን ለመፈጸም አይችልም፡፡

**አንቀጽ 228 የዕድሜ ማስረጃ**

1. የአንድ ሰው ዕድሜ የሚረጋገጠው በልደት ምስክር ወረቀት ነው፡፡
2. የልደት ምሥክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ ዕድሜውን በአስተማማኝነት ለማረጋገጥ ያስችላሉ በሚባሉ ሰነዶች ወይም ከሁለት ያላነሱ ምስክሮች ቃል መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤት ዕድሜውን ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 229 ውሣኔ ሰጭ አካላት መከተል ስላለባቸው መርህ**

በዚህ ምዕራፍ መሠረት በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሣኔዎች ሁሉ ለልጆች ደህንነትና መልካም አስተዳደግ የሚበጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል ሁለት
## አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ
## ስለሚጠብቁ ተቋማት

**አንቀጽ 230 የወላጆች ስልጣን**

አባትና እናት ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉ አካለመጠን ላልደረሱት ልጆቻቸው የአሣዳሪነትና የሞግዚትነት የጋራ ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ 231 ከወላጆቹ የአንዱ ብቁ አለመሆን**

1. ከወላጆቹ አንዱ የሞተ፣ችሎታ ያጣ፣ የተገቢነት መብት ያጣ ወይም ከቤተሰብ አስተዳዳሪነት መብቱ የታገደ እንደሆነ የአሣዳሪነትና የሞግዚትነት ስልጣኑን ይዞ የሚቆየው አንደኛው ወገን ብቻ ይሆናል፡፡
2. እንዲሁም የልጁ አባት ያልታወቀ በሆነ ጊዜ የዚህን ስልጣን ሥራ የምትፈጽመው እናቱ ብቻ ትሆናለች፡፡

**አንቀጽ 232 የልጆቹ አባትና እናት መፋታት**

1. በዚህ ህግ በአንቀጽ 88 መሠረት ባልና ሚስት በስምምነት ሲፋቱ የልጆቻቸውን አሣዳሪነትና ሞግዚትነት በተመለከተ በስምምነት ይወስናሉ፡፡
2. በማናቸውም የፍቺ ሁኔታ የልጆቻቸውን አሣዳሪነትና ሞግዚትነት ባልና ሚስቱ በስምምነት ሊወስኑ ካልቻሉ ፍቺውን የወሰነው ፍርድ ቤት ስለልጆቹ አሣዳሪነትና ሞግዚትነትም አብሮ ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 233 በኑዛዜ ቃል ስለተመረጠ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት**

**1. *መሠረቱ***

1. አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ በህይወት ያለ ወላጅ ከጊዜ ሞቱ በኋላ ልጁን የሚያስተዳድርለትን ወይም ለልጁ ሞግዚት የሚሆነውን ሰው በመጨረሻ የኑዛዜ ቃል ለመምረጥ ይችላል፡፡
2. እንዲሁም የአሣዳሪውን ወይም የሞግዚቱን ስልጣን ለመወሰንና የአሣዳጊነቱን የሥራ አመራር ስልጣን በተወሰነ ሁኔታ ብቻ ለመስጠት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 234 – 2 አሣዳሪ ወይም ሞግዚት ለመሾም የሚፈጸም ግዴታ**

አባት ወይም እናት በህይወት ሳለ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ የአሣዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ ያካሄድ የነበረ ካልሆነና በዚሁም ጊዜ በገዛ ፈቃዱ ስልጣኑን አውቆ የተወከለ ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በላይ በአንቀጽ 233 ለአባት ወይም ለእናት የተሰጠው መብት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 235 ለፍርድ ቤት አቤቱታ ስለማቅረብ**

አካለ መጠን ያልደሰው ልጅ ጥቅም የሚያስገድድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ስለ አሣዳሪው ወይም ስለ ሞግዚቱ አባቱ ወይም እናቱ ያደረጉትን ውሣኔ ፍርድ ቤት ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 236 የልጁን አሣዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ስልጣን ሊይዙ የሚገባቸው ዘመዶች**

1. **ሊከተሉት ስለሚገባ ቅደም ተከተል**

አንድ ልጅ አባትና እናት የሌለው እንደሆነና ከሁለቱ በመጨረሻ የሞተው ወላጅ በሚገባ ሁኔታ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት ሣያደርግለት ቀርቶ አንደሆነ ለልጁ አሣዳሪነት ወይም ሞግዚትነት በሕጉ መሠረት የሚመረጡትና ይህ ስልጣን የሚሰጣቸው ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሰዎች ናቸው፡-

ሀ. የልጁ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፣

ለ. እነዚህ በሌሉ ጊዜ አካለመጠን የደረሱ የልጁ ወንድሞች ወይም እህቶች፣

ሐ. እነዚህ በሌሉ ጊዜ የልጁ አጎት ወይም አክስት፡፡

**አንቀጽ 237 – 2 ይህ ቅደም ተከተል ስለሚለወጥበት ሁኔታ**

www.abyssinialaw.com

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ስልጣን በሚሰጠው ሰው ምትክ ለልጁ የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ማንኛውም ሰው የአሣዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ስልጣን ለእኔ ይሰጠኝ ሲል ጥያቄ ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. ይህን ጥያቄ መቅረብ የሚገባው ቅደም ተከተሉ ለሚመለከታቸው ዘመዶች ሲሆን በመካከላቸው ስምምነት ካልተገኘ ግን ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ይቀርባል፡፡
3. ጥያቄው መቅረብ ያለበት አሣዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህንን ስልጣን መያዙ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡
4. ጥያቄውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል መሠረት የሚሆነው የልጁ ደህንነትና ጥቅም ሊሆን ይገባል፡፡

**<u>አንቀጽ 238 በሕግ የሚመረጡ ዘመዶች መታጣት</u>**

1. ከዚህ በላይ ባሉት አንቀጾች የተመለከተውን መሠረት በማድረግ ለልጁ አንደ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት ለማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ይህ ሥራና ስልጣን ፍርድ ቤት ለመረጠው ሰው ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ይህንን ጉዳይ ለመወሰን የልጁ ዘመድ በሆነ ወይም ባልሆነ ያገባኛል ባይ በሚቀርብ ጥያቄ ሊመሠረት ይችላል፡፡
3. የህፃናትን ደህንነት ለመከታተል ስልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካልም ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 239 የፍርድ ቤቱ ምርጫ 1. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች</u>**

ፍርድ ቤት ለልጁ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሆን የሚመርጠውና ይህንን ስልጣን የሚሰጠው የልጁ የቅርብ የስጋ ዘመድ የሆነን ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለውንና በተቻለ መጠንም ይህንኑ ሥራ ለማከናወን ችሎታና ፈቃደኛነት ያለውን ሰው ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 240 – 2 የበጐ አድራጐት ድርጅት</u>**

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የአሣዳሪነቱን ወይም የሞግዚትነቱን ስልጣን ለዚህ አይነቱ ጉዳይ ለተቋቋመ የበጎ አድራጐት ድርጅት ሊሰጥ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 241 ተመሣሣይ ሁኔታዎች</u>**

ከዚህ በላይ ለተጻፉት ድንጋጌዎች አፈጻጸም አንድ ሰው በሕግ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የአሣዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ተግባሮቹን ለማከናወን የማይችል የሆነ እንደሆነ እንደሌለ ይቆጠራል፡፡

**<u>አንቀጽ 242 የአሣዳሪው ወይም የሞግዚቱ መታወቂያ</u>**

1. በመሠረቱ አካለመጠን ያልደረሰው ሰው ልጅ አሣዳሪ እንዲሆን ስልጣን ተሰጥቶት የልጁን አሣዳሪነት የተቀበለው ሰው ሞግዚቱም ነው፡፡
2. የነገሩ ሁኔታ ተቃራኒ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በህይወት ያለው አባት ወይም እናት ወይም ፍርድ ቤት ለልጁ የሚሾመው ሞግዚት ወይም አሣዳሪ ሁለቱንም ስልጣኖች እንደያዘ ይቆጠራል፡፡

**<u>አንቀጽ 243 ለአባትና ለእናት ስለተሰጠ መብት</u>**

አባት ወይም እናት ጉዳዩ ጠቃሚ መስሎ የታያቸው እንደሆነ የልጃቸውን የአሣዳሪነት ስልጣን ራሣቸው ይዘው ሞግዚቱን ለመሾም ይችላሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 244 ለፍርድ ቤት የተሰጠ ስልጣን</u>**

ፍርድ ቤት የልጁን አሣዳሪና ሞግዚት የመሾም ስልጣን በያዘበት ጊዜና ይህንን ለማድረግ አሣማኝ ምክንያት ሲኖር ከአሣዳሪው በተጨማሪ ሌላ ሞግዚት ለመሾም ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 245 ስለ ምትክ ሞግዚት</u>**

1. **<u>በሞግዚቱ እና አካለ መጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል ስለሚነሳ የጥቅም ግጭት</u>**

1. በሞግዚቱ እና አካለ መጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል ስለሚነሣ የጥቅም ግጭት የተነሳ እንደሆነ ፍርድ ቤት አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ምትክ ሞግዚት ይሾምለታል፡፡
2. ምትክ ሞግዚት የሚመረጠው በሞግዚቱ ወይም ወደ ላይ ከሚቆጠሩት የልጁ ወላጆች ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በአንዳቸው ጥያቄ አቅራቢነት ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 246 – 2 አካለ መጠን ባልደረሱ በብዙ ልጆች መካከል ስለሚነሣ የጥቅም ግጭት</u>**

1. አካለ መጠን ባልደረሱ በብዙ ልጆች መካከል የጥቅም ግጭት የተፈጠረ እንደሆነና የነዚህም ተጠሪ ወኪል አንድ የጋራ ሞግዚት ብቻ በሆነ ጊዜ ከዚህ በላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ /አንቀጽ 245/
2. የጥቅም ግጭቱ የሚፈታውም በሞግዚቱና በምትክ ሞግዚቱ መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ይሆናል፡፡

www.abyssinialaw.com

**አንቀጽ 247 የሥራው አጀማመር**

1. የአሣዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የሚጀመረው አሣዳሪው ወይም ሞግዚቱ በሕጉ መሠረት ወይም በፍርድ ውሣኔ ተመርጦ እንደተሾመ ወዲያውኑ ነው፡፡
2. ሆኖም የአሣዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ የተሰጠው መሆኑን ከማወቁ በፊት አሣዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህንን ስራውን ሣይጀምር ለደረሰው ጉዳት ሁሉ በሀላፊነት ሊጠየቅ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 248 ሥራው የግዴታ ስለመሆኑ**

የአሣዳሪነትን ወይም የሞግዚትነትን ሥራዎች እንዲያከናውን ተመርጦ የተሾመው ሰው ሥራውን የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 249 ሥራው እንዲቀርለት ስለሚቀርብ ጥያቄ**

1. አንድ ሰው የአሣዳሪነትን ወይም የሞግዚትነትን ተግባር ማከናወኑ በራሱ፣ላይ ከበድ ያሉ ችግሮችን በአጠቃላይ ኑሮውም ላይ እንቅፋት የሚያስከትልበት ከሆነ ሥራው እንዲቀርለት ፍርድ ቤት ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. እንዲሁም በተመሣሣይ ሁኔታ አሣዳሪው ወይም ሞግዚቱ ከተሰጠው የአሣዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራው እንዲሻር ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 250 በሕግ አግባብ የሚሰጥ ልዩ አስተያየት**

በዚህ ሕግ መሠረት ለአሣዳሪነት ወይም ለሞግዚትነት ስለሚመረጡ ሰዎች የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ የሚከተሉት ሰዎች በአሣዳሪነት ወይም በሞግዚትነት እንዳይሾሙ ወይም እንዲሻሩ ጥያቄ ካቀረቡና ይህም ጥያቄ የራሣቸውን ልጆች የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር የአሣዳሪነትን ወይም የማግዚትነትን ስራ እንዲሠሩ አይገደዱም፡-

ሀ. ዕድሜው 65 ዓመት የሞላ ሰው፣
ለ. በውትድርና የተሰማሩ ሰዎች፡፡

**አንቀጽ 251 ለጊዜው ሥራውን የማከናወን ግዴታ ስለመኖሩ**

1. የልጁ አሣዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ ችግር ያደርስብኛል ብሎ ምክንያት በማቅረብ ይህ ኃላፊነት እንዲወገድለት የሚጠይቅ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት በዚህ ሥራ ሌላ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት ተተክቶ ስልጣኑን እስኪረከብ ድረስ የተሰጠውን ሥራ ለጊዜው የማከናወን ግዴታ አለበት፡፡
2. እንዲሁም በሹመቱ ላይ ተቃውሞ የተነሣበት አሣዳሪ ወይም ሞግዚትም ተመሣሣይ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 252 ስለሥራው መቅረት**

1. የአሣዳሪው ወይም የሞግዚቱ ሥራዎች ቀሪ የሚሆኑበት የሚጠበቀው ልጅ የሞተ እንደሆነ ወይ አካለመጠን በደረሰ ጊዜ ወይም ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ በወጣ ጊዜ ነው፡፡
2. እንዲሁም አሣዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሲሞት ወይም ችሎታ ሲያጣ ወይም ብቁ ያለመሆኑ ሲገለጽ ወይም ከስራዉ ሲሻር ቀሪ ይሆናል፡፡
3. በመጨረሻም አዲስ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት አካለመጠን ለደረሰው ልጅ ሲሾምለትም የቀድሞዎቹ ተሿሚዎች ኃላፊነት ያበቃል፡፡

**አንቀጽ 253 ችሎታ ማጣት 1. አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ**

የራሱን ልጆች በሚመለከት ጉዳይ ካለሆነ በስተቀር አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ የአሣዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማካሄድ ችሎታ የለውም፡፡

**አንቀጽ 254 - 2 በፍርድ የተከለከሉ ሰዎች**

1. በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው የአሣዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማከናወን አይችልም፡፡
2. ይህንኑ ሥራ ያከናውን የነበረ አንድ ስው ችሎታ ያጣ መሆኑ በፍርድ ቤት ውሣኔ የተገለጸ እንደሆነ በሕግ መሠረት የተከለከለውን ሰው ሥራ ተረክቦ በምትክነት ለማካሄድ ለሚገባው ሰው የዚህ ሰው ሞግዚት ወዲያውኑ ማስታወቅ አለበት፡፡
3. እንዲህ ያለ ሰው የሌለም እንደሆነ በፍርድ የተከለከለው ሰው ምትክ እንዲደረግለት ሞግዚቱ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅርብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 255 ብቁ ስላለመሆን**

1. አንድ ሰው የአሣዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማካሄድ ብቁ አይደለም ብሎ ፍርድ ቤት ለመወሰን የሚችለው የወንጀል ተግባር በመፈጸሙ የግል ነፃነትን የሚከለክል የእስራት ወይም የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሲሆን ነው፡፡
2. ፍርድ ቤት የዚህን አይነት ቅጣት በአንድ ሰው ላይ በሚወስንበት ጊዜ ነገሩ ተገቢ መሆኑን የገመተ እንደሆነ የተፈረደበት ሰው ለዚህ ሥራ ብቁ አለመሆኑን ጭምር ለመወሰን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 256 – 1 የአሣዳሪው መሻር**

www.abyssinialaw.com

1. አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ አሣዳሪ እንዲሆኑ የተሾመ ሰው ልጅ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነውን ጥበቃ ሣያገኝ ወይም ከሞራል ጋር የሚስማማ የአእምሮ አስተዳደግ ወይም ከችሎታው ጋር ተመዛዛኝ የሆነ ትምህርት እንዲያገኝ ሣያደርግለት የቀረ እንደሆነ አሣዳሪው እንዲሻር ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል፡፡
2. ይህንንም ውሣኔ ለመስጠት አሣዳሪው የሚኖርበትን የአካባቢ ሁኔታና ጊዜውንም መመርመርና መሠረት የማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡
3. በተለይም ፍርድ ቤቱ አሣዳሪውን ለመሻር የሚችለው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወንጀል መሥራቱ የተረጋገጠ ሲሆንና ይህንንም ወንጀል የፈጸመው በመጥፎ አስተዳደግ ወይም በአሣዳሪው ጉድለት ተገቢውን የግብረገብነት ትምህርት ለማግኘት ባለመቻሉ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 257 – 2 የሞግዚቱ መሻር</u>**

አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ ሞግዚት የሆነ ሰው እንዲሻር ፍርድ ቤት የሚወሰነው ሞግዚቱ የልጁን ንብረትና ሀብት በመጥፎ ሁኔታ ያስተዳደረና አጠባበቁም በቂ ያልሆነ እንደሆነ ወይም ልጁን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድር ስልጣን የሰጠው ሰው ወይም አካል የሰጠውን መመሪያና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ሣይጠብቅና ሣይፈጽም የቀረ እንደሆነ ወይም እዳ ለመክፈል ያለመቻሉ በፍርድ ውሣኔ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 258 – 3 የወላጆች መሻር</u>**

1. የልጁ አባት ወይም እናት ወይም ሌሎች ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹ ከልጃቸው አሣዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ሥራቸው እንዲሻሩ መወሰን ሲያስፈልግ ፍርድ ቤቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሣኔ በተሻረው ወገን ጠያቂነት በማንኛውም ጊዜ እንደገና ሊመረምረው ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 259 – 4 ሥነ-ሥርዓት</u>**

1. አንድ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሻር የሚቀርበው ጥያቄ በማናቸውም በጉዳዩ ያገባኛል ባይ ወገን ወይም በዐቃቤ ሕግ በኩል ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ አሣዳሪውን ወይም ሞግዚቱን ለመሻር ከመወሰኑ በፊት በርሱ በኩል ያለውን ሀሣብ ሊያዳምጠው ይገባል፡፡
3. ሆኖም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተውን ሲያከናውን በልጁ ደህንነት ወይም ሀብት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ይደርሣል ተብሎ የሚገመት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ጊዜያዊ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 260 የፍርድ ቤት ኃላፊነት</u>**

1. ፍርድ ቤት አንድን ሰው አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ አሣዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ለመሾም ሲመርጥ ወይም የተሾመውን ከሥራው ሲሽር ከውሣኔው በፊት በተቻለ መጠን ከልጁ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፣አካለመጠን ከደረሱ ወንደሞቹና እህቶቹ ጋር መመካከር ይገባዋል፡፡
2. አስፈላጊ መስሎ ሲታየውም አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ያለውን ሀሣብ ሊያዳምጥ ይችላል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ ውሣኔውን ሲሰጥ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም የማይጓደልበትን አሠራር ብቻ መከተል እንጅ የቀረቡለትን ሃሣቦች ሁሉ የመቀበል ግዴታ አይኖርበትም፡፡

**<u>አንቀጽ 261 ሥራው ያለ ክፍያ የሚከናወን ስለመሆኑ</u>**

1. የአሣዳሪነትና የሞግዚትነት ሥራ የሚከናወነው ማናቸውም ዋጋ ሣይከፈልበት በነፃ ነው፡፡
2. ሆኖም አሣዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሥራውን ለማከናወን ረጅም ጊዜ የሚጠይቀው የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ አንድ የተወሰነ አበል ሊቆረጥለት ይችላል፡፡
3. ይኸውም አበል አካለመጠን ካልደሰው ልጅ የሀብት ገቢ ላይ ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ሀብት ሊወስድ አይችልም፣የአበሉም ልክ ከጠቅላላው የሀብት ገቢ ሲሶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 262 የሥራው አካሄድ የግል ስለመሆኑ</u>**

1. የአሣዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የግል ጠባይ የያዘ ስለሆነ ሥራውን የሚያከናውነው ያው ራሱ እንጅ ለአሣዳሪው ወይም ለሞግዚቱ ወራሾች ሊተላለፍ አይችልም፡፡
2. ወራሾቹ በኃላፊነት የሚጠየቁት አሣዳሪው ወይም ሞግዚቱ በፈጸመው የሥራ አካሄድ ጉድለት ብቻ ነው፡፡ ይኸውም በውርስ ሕግ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 263 የወራሾች ግዴታ</u>**

1. የአንድ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት ወራሾች አሣዳሪው ወይም ሞግዚቱ እንደሞተ ወዲያውኑ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 236 ሥር በተመለከተው መሠረት ለሟቹ ምትክ ሊሆን ለሚገባው ሰው የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡
2. የዚህ አይነት ሰው የሌለ እንደሆነ በሟቹ ምትክ የሚመረጠው ሰው እንዲሾም ለፍርድ ቤት ማስታወቅ አለባቸው፡፡

www.abyssinialaw.com

3. የአሣዳሪው ወይም የሞግዚቱ ወራሾች ከዚህ በላይ ባሉት ንዑሣን አንቀጾች ሥር የተመለከቱት ግዴታዎች እስከወጡ ድረስ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅም ሆነ ለሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ኃላፊዎች ሆነው ይቆያሉ፡፡

**አንቀጽ 264 የአሣዳሪነትና የሞግዚትነት ማስረጃ**

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አሣዳሪነቱን ወይም ሞግዚትነቱን የሚያስረዳለት ጽሁፍ እንዲሰጠው አሣዳሪው ወይም ሞግዚቱ ፍርድ ቤት ለመጠየቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 265 ከሞግዚት ጋር የሚመሳሰል ሁኔታ**

ሞግዚትን የሚመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚት ጉዳይም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የአሣዳሪውና የሞግዚቱ ስልጣን
## ንዑስ ክፍል አንድ
## አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ

**አንቀጽ 266 አሣዳሪው የመንግሥት ተቋማትን እገዛ መጠየቅ ስለመቻሉ**

አሣዳሪው ከዚህ በታች በተመለከቱት አንቀጾች የተስጠዉን ስልጣን በሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል አግባብነት ያላቸውን የመንግሥት ተቋማት እገዛ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 267 አካለ መጠን ስላልደሰ ልጅ መኖሪያ ቦታ**

1. አሣዳሪው አካለ መጠን ያልደሰውን ልጅ መኖሪያ ቦታ ይወስናል፡፡
2. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ያላሣዳሪው ፈቃድ የተመደበለትን መኖሪያ ቦታ ሊተው አይችልም፡፡
3. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የተመደበለትን መኖሪያ ቦታ ትቶ የሄደ እንደሆነ አሣዳሪው ወደ መኖሪያ ቦታው እንዲመለስ ሊያስገድደው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 268 አካለ መጠን ስላልደረሰ ልጅ ጤና አጠባበቅ**

1. አሣዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ የጤንነት ሁኔታ ይከታተላል፡፡
2. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሲታመም ከህመሙ እንዲፈወስ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል፡፡

**አንቀጽ 269 አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግ**

1. አሣዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ አስተዳደግ ይመራል፡፡
2. አሣዳሪው አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መልካም አስተዳደግ ተገቢነት ያለውን የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 270 አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት**

1. አሣዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ማህበራዊ ግንኙነቶች ይመራል፣ይቆጣጠራል፡፡
2. ሆኖም አሣዳሪው በቂ ምክንያት ሣይኖረው ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ ሊያግደው አይችልም፡፡

**አንቀጽ 271 አጠቃላይ የሙያ ትምህርት የመስጠት ግዴታ**

አሣዳሪው አካለ መጠን ላልደረስው ልጅ እድሜና ችሎታ ተመጣጣኝ የሆነ አጠቃላይ ትምህርት ወይም የሙያ ስልጠና እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፡፡

**አንቀጽ 272 አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ 1. መሠረቱ**

1. አሣዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች በመቀበል ለልጅየው ጥቅም ያውላል፡፡
2. አሣዳሪው ገንዘቡን ለምን አገልግሎት እንዳዋለው መግለጫ ለመስጠት አይገደድም

**አንቀጽ 273 – 2 ከፍተኛ ስለሆነ ገቢ**

1. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ ከፍተኛ ሲሆንና አሣዳሪው የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤት ከዚህ በላይ በአንቀጽ 272 ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ እንዳይሆን ሊያግድ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ትእዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ አካመጠን ላልደረሰው ልጅ ለአስተዳደጉና ለትምህርቱ በቂ ነው የሚለውን የገንዘብ መጠንና የሚከፈልበትን ጊዜ በመወሰን ለአሣዳሪው እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡
3. ተራፊውን ገንዘብ በአትራፊ ሥራ ላይ እንዲያውለው በሞግዚቱ እጅ ተቀማጭ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 274 – 3 አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ከሥራው ስለሚያገኘው ገቢ**

1. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ እድሜው ከ14 አመት በላይ ሲሆን ከስራው የሚያገኘውን ገቢ እራሱ ይቀበላል፡፡
2. ለራሱ ቀለብ የሚሆነውን ለአሣዳሪው ከሰጠ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ በዚህ ሕግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሊጠቀምበት ሙሉ ነፃነት አለው፡፡

www.abyssinialaw.com

**አንቀጽ 275 – 4 በስጦታ ወይም በውርስ ስለተላለፋ ሀብቶች**

1. አካለ መጠን ላልደሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ሀብት የሚያስተላልፍ ማናቸውም ሰው ልጁ አካለመጠን ሣይደርስ አሣዳሪው ተቀብሎ ጥቅም ላይ እንዳያውለው አስቀድሞ ሊያዝ ይችላል፡፡
2. በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው ውስጥ ስለ ንብረቱ አስተዳደርና ስለሚገኘውም ገቢ የተመለከቱ ኃይለ ቃሎች ተፈጻሚ መሆን አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 276 የመክፈያ ጊዜአቸው ያልደረሰ ገቢዎች**

የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሰ ገቢዎችን አሣዳሪው ግዴታ ሊገባባቸው አይችልም፡፡

**አንቀጽ 277 ስለ ወላጆች ስልጣን**

1. አካለ መጠን ያልደሰው ልጅ አባትና እናት በጋራ አሣዳሪዎቹ በሆኑ ጊዜ የአሣዳሪነት ተግባራቸውን በመመካከርና በመግባባት ይወጣሉ፡፡
2. አባት እና እናት ያለመግባባታቸው በግላቸው ወይም በሽምግልና ለመፍታት ያልቻሉ እንደሆነ ከሁለቱ አንደኛው በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ውሣኔ ይሰጣል፡፡
3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ ሥር የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አባትና እናት በአሣዳሪነታቸው በሚሰጡት ውሣኔ ላይ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

**አንቀጽ 278 የወላጆች መለያየት**

ወላጆች በመለያየታቸው ምክንያት የአሣዳሪነቱ ስልጣን የአንደኛው ወላጅ ብቻ የሆነ እንደሆነ ይኸው ወላጅ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ የአሣዳሪነት ተግባር በማከናወን ላይ የሌለው ወገን ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም አካለ መጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው ለፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 279 አሣዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ በማይሆንበት ጊዜ**

አሣዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ ያልሆነ እንደሆነ በልጁ አስተዳደግ ረገድ የሚሰጠው ውሣኔ ላይ ከወላጆቹ አንዳቸው ወይም ሌላ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሰው ወይም ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር

**አንቀጽ 280 መሠረቱ**

1. ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በተመለከተ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ይወከላል፡፡
2. ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በማስከበርና በማስተዳደር ረገድ ሞግዚቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 281 የንብረት ቆጠራና የዋጋ ግምት ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን ከጀመረ በኋላ**

1. የሞግዚትነቱን ሥራ ከጀመረ በኋላ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሞግዚቱ ሶስት ምስክሮች ባሉበት አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ይቆጥራል፤የዋጋውንም ግምት ያወጣል፡፡
2. ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ የሚጠይቀው እዳ ሲኖር በንብረት ቆጠራው መዝገብ በወቅቱ ካላሰፈረው በስተቀር የእዳው ክፍያ ቀሪ ይሆንበታል፡፡

**አንቀጽ 282 – 2 አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የውርስ ሀብት**

1. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወራሽ በሚሆንበት ጊዜ ሞግዚቱ ስለልጁ ሆኖ ውርሱን ከመቀበሉ አስቀድሞ ሶስት ምስክሮች ባሉበት የውርስ ንብረቱን ቆጠራ ያከናውናል፣የዋጋውንም ግምት ያወጣል፡፡
2. ሞግዚቱ ከውርሱ ሀብት ውስጥ ድርሻ ያለው ሆኖ ይህንኑ በንብረት ቆጠራው መዝገብ ያላሰፈረው እንደሆነ ድርሻው ቀሪ ይሆንበታል፡፡
3. የንብረት ቆጠራው ባለመከናወኑ ወይም በአግባቡ ባለመሠራቱ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት ሞግዚቱ በኃላፊነት ይጠየቅበታል፡፡

**አንቀጽ 283 የሞግዚቱ ንብረት አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ ንብረት ጋር መቀላቀል የሌለበት ስለመሆኑ**

1. ሞግዚቱ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት ከግል ንብረቱ ጋር እንዳይቀላቀል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡
2. በተለይም አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገንዘብ ሞግዚቱ በራሱ የባንክ ሂሣብ ማስቀመጥ ወይም እንዲቀመጥ ማድረግ አይፈቀድለትም፡፡

**አንቀጽ 284 የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ውድ እቃወች ስለሚመጡበት ሁኔታ**

አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በማስተዳደር ረገድ ችግር የሚፈጥር ካልሆነ በስተቀር የገንዘብ ሠነዶችን፣ውድ እቃዎችን፣ ጠቃሚ ጽሁፎችንና ሌሎች ተመሣሣይ ነገሮችን ሁሉ ሞግዚቱ ሊጠፉ ወይም ሊባክኑ በማይችሉበት አስተማማኝ ስፍራ ማስቀመጥ አለበት፡፡

**አንቀጽ 285 የፍርድ ቤት ስልጣን**

www.abyssinialaw.com

1. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሞግዚት የልጁ ወላጅ ባልሆነ ጊዜ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት መልካም አስተዳደር በሚመለከት ለሞግዚቱ መመሪያ እንዲሰጥ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ የልጁ ወላጆች ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹ ወይም እህቶቹ አንዳቸው ወይም ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱም አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አጠቃላይ ሁኔታ የሞግዚቱን ችሎታና የልጅየውን ጥቅም በማመዛዘን ስለሀብቱ አስተዳደር ጠቃሚ መስሎ የሚታየውን መመሪያ ይሰጠዋል፡፡

**<u>አንቀጽ 286 አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ስለሚተላለፍ ንብረት</u>**

1. አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ንብረት የሚያስተላልፍ ሰው የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት ተገቢ ናቸው የሚላቸውን የአሠራር መመሪያዎች ሞግዚቱ እንዲከተል ሊያዘው ይችላል፡፡
2. የአሠራር መመሪያዎቹን ተከትሎ ለመሥራት የማይቻል ወይም አካለ መጠን ባልደረሰው ልጅ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስበት መስሎ የታየው እንደሆነ ሞግዚቱ መመሪያዎቹ እንዲስተካከሉለት ፍ/ቤትን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 287 ስለ ንግድ ደርጅቶችና ሌሎች መሠል ድርጅቶች</u>**

1. የንግድ፣ ኢንዱስትሪ ወይም ሌሎች መሰል ድርጅቶች አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት አካል የሆኑ እንደሆነ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው በሚያቀርቡት ጥያቄ የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነው ሞግዚት ንብረቱን እንዲያጣራ ወይም እንዳለ እንዲቀጥል እንዲያደርግ ፍርድ ቤት ሊያዘው ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ይህንን ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ሞግዚትነቱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ፣የሞግዚቱን ችሎታና አካለ መጠን ያልደሰውን ልጅ ጥቅም ከግምት ውስጥ ማስግባት አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 288 አንዳንድ ንብረቶችን ስለመሸጥ</u>**

1. ሞግዚቱ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑትንና የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን አክሲዮናችንና የገንዘብ ሠነዶችን ለመሸጥ ይችላል፡፡
2. በልጁ አባት ወይም እናት ላይ ካልሆነ በስተቀር በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማናቸውም ሰው ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤት ስለሽያጩ መመሪያ ለመስጠት ወይም ሽያጩ እንዳይካሄድ ለመከልከል ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 289 ለአምጭው እንዲከፈል ስለሚሉ ሰነዶች</u>**

1. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አባት ወይም እናት ያልሆነ ሞግዚት ለአምጭው እንዲከፈል የሚሉ ሰነዶች የልጁ ሀብቶች ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲሸጡ ወይም በልጁ ስም በተመዘገቡ ሰነዶች እንዲለወጡ ማድረግ አለበት፡፡
2. ሞግዚቱ ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ ከተመለከተው ግዴታ ነፃ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 290 እዳዎችና ገቢ ገንዘቦች</u>**

1. ሞግዚቱ አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ እዳዎች ካሉ ከልጁ ሀብት በመቀነስ ይከፍላል፡፡
2. አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ መከፈል የሚገባውን ካፒታል እና ሌሎች ገቢዎች ይቀበልለታል፣ስለመቀበሉም በማረጋገጥ ደረሰኝ ይሰጣል፡፡

**<u>አንቀጽ 291 ካፒታልን አትራፊ በሆነ ሥራ ላይ  ስለማዋል</u>**

1. **<u>የሞግዚቱ ግዴታ</u>**

1. የገንዘቡ መጠን ከ500 ብር በላይ የሆነን አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ካፒታል ሞግዚቱ አትራፊ በሆነ ሥራ ላይ ማዋል አለበት፡፡

2. ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 292 – 2 የጊዜ ገደብ</u>**

1. ካፒታሉ በሞግዚቱ እጅ በገባ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ  በአትራፊ ሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የጊዜውን መጠን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 293 ስለ ኃላፊነት</u>**

1. በአትራፊ ሥራ ላይ ላላዋለው ገንዘብ ሞግዚቱ ሕጋዊ ወለዱን አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ መክፈል አለበት፡፡
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተጨማሪ የጉዳት ካሣ እንዲከፍል ሊፈርድበት ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 294 ገቢዎች</u>**

1. አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች፣በቂ ሆነው የማይገኙ ሲሆንም ከሀብቱ ቀንሶ ለአስተዳደጉና ለትምህርቱ አገልግሎት እንዲያውል ሞግዚቱ  ለአሣዳሪው ይሰጠዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

2. ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር ለዚሁ አገልግሎት የሚውለው ገንዘብ በየወሩ ለአሣዳሪው ይከፈላል፡፡
3. የአከፋፈሉም ሁኔታ በአሣዳሪውና በሞግዚቱ ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሣኔ መሠረት ሊሻሻል ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 295 ስለ ኪራይ ውሎች</u>**

በፍርድ ቤት ፈቃድ የተደረጉ ካልሆኑ በስተቀር ሞግዚቱ የሚያደርጋቸው የኪራይ ውሎች ልጅየው አካለ መጠን ከደረሰ ከሶሶት አመታት በኋላ እንዲፈጽማቸው አይገደድም፡፡

**<u>አንቀጽ 296 ስለ ውርስ</u>**

1. ልጁ በውርስ የሚያገኘውን ንብረት ሞግዚቱ ይቀበላል፡፡
2. ሞግዚቱ የውርስ ሀብት እዳውን ለመክፈል ፈጽሞ የማይችል ካልሆነ በስተቀር ዉርሱን አልፈልግም ለማለት አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 297 ስለስጦታ</u>**

1. አካለ መጠን ስላልደረሰው ልጅ የሚሰጠው ስጦታ ጠቃሚነት የለውም በማለት ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ አልቀበልም ለማለት አትችልም፡፡
2. በተለምዶ ከሚሰጡ አነስተኛ ስጦታዎች ውጪ ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በልጁ ስም በስጦታ ለመስጠት አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 298 የዋስትና ግዴታ መግባት የማይቻል ስለመሆኑ</u>**

ሞግዚቱ አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለሌላ ሰው እዳ በዋስትና ሊያስይዝ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 299 ስል ግልግል</u>**

ክርክር የሚደረግበት ጥቅም ከአንደ ሺህ ብር ያነሰ ካልሆነ ወይም አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም በሚመለከት ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 300 ሞግዚቱ አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር ስለሚያደርጋቸው ውሎች</u>**

1. ሞግዚቱ ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለመግዛት፣በኪራይ ለመጠቀም ወይም ሌላ ማናቸውንም ውል ከእርሱ ጋር ለመፈጸም አይችልም፡፡
2. እንዲሁም ሞግዚቱ በፍርድ ቤት ካልተፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ማናቸውንም መብት ወይም ገንዘብ የሚጠይቅበትን መብት ለመቀበል አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 301 ስለ ብድር</u>**

ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ስም የብድር ውል ለመዋዋል አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 302 አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር መመካከር ስለማስፈለጉ</u>**

1. አካለ መጠን ያልደሰው ልጅ እድሜ ከአሥራ አራት አመት ያነሰ ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ የልጁ እድሜ በሚፈቅድለት መጠንና እርሱን የሚመለከቱ ከፍተኛ ጉዳዩች በተነሱ ጊዜ አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ማማከር አለበት፡፡
2. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ፈቃዱን መስጠቱ ሞግዚቱን ከተጠያቂነት አያድነውም፡፡

**<u>አንቀጽ 303 ሞግዚቱ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ እንዲሠራ ስለሚሰጠው ፈቃድ</u>**

**1. <u>*መሠረቱ*</u>**

1. አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ እድሜና የገንዘብ አቅም መሠረት በማድረግ የእለት ጉዳዩችን የሚመለከቱ ውሎችን ብቻ እንዲያደርግ ሞግዚቱ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡
2. ይኸው ፈቃድ በዝምታም ቢሆን ሊሰጥ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 304 – 2 የእለት ጉዳዮች</u>**

1. ድርጊቱ እንዲፈጸም የፍርድ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልገው እንደሆነ በምንም መንገድ የእለት ጉዳይ ሊባል አይችልም፡፡
2. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ከ300 ብር በላይ ግዴታ እንዲገባ የሚያስገድደው ሲሆን ድርጊቱ የእለት ጉዳይ ነው ሊባል አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 305 በሞግዚቱ ላይ ስለሚኖረው ውጤት</u>**

አካለ መጠን ያልደሰው ልጅ በሞግዚቱ ፈቃድ ለሚገባቸው ግዴታዎች ሞግዚቱ ለሶስተኛ ወገኖች ዋስ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 306 ስለኑዛዜ</u>**

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ኑዛዜ ሊያደርግ አይችልም፡፡
2. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ 16 አመት ሣይሞላው ኑዛዜ ማድረግ አይችልም፡፡
3. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ 16 አመት ሣይሞላው የሚያደርገው ኑዛዜ 16 አመት ከሞላው በኋላ ባይሰርዘውም ውጤት አይኖረውም፡፡

**<u>አንቀጽ 307 ንብረት ለማስተዳደር ሞግዚት ስለሚያደርገው ወጪ</u>**

www.abyssinialaw.com

ሞግዚቱ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ሲል ከግሉ የሚያወጣቸው ወጪዎች እንዲተኩለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

**<u>አንጽ 308 አካለ መጠን ስላልደረሰው ልጅ ሀብት አስተዳደር ሪፖርት ማቅረብ ስለማስፈለጉ</u>**

1. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አስተዳደር ሁኔታ ሂሣቡን የሚያመለክት ሪፖርት አዘጋጅቶ መያዝ አለበት፡፡
2. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን የደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በጋራ ወይም በተናጠል ጥያቄ ሲያቀርቡለት ሞግዚቱ የአስተዳደርና የሂሣብ ሪፖርቱን እንዲመለከቱት ይደረጋል፡፡

**<u>አንቀጽ 309 ተፈጻሚነት</u>**

በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 275 እስከ 277 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለሞግዚትም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን</u>**

**<u>ደንቦች መጣስ ስለሚያስከትለው ውጤት</u>**

**<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>**

**<u>አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሥራዎች</u>**

**<u>አንቀጽ 310 መሠረቱ</u>**

አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ከስልጣኑ በላይ የሚፈጽማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ፈራሾች ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 311 እንዲፈርሱ ስለመጠየቅ</u>**

አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ የፈጸማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች እንዲፈርሱ መጠየቅ የሚችሉት አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ራሱ ወይም ወራሾቹ ወይም ወኪሎቹ ናቸው፡፡

**<u>አንቀጽ 312 ስለ ተዋዋዩ ቅን ልቡና</u>**

1. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 310 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ሌላኛው ተዋዋይ ወገን ከልጁ ጋር የተዋዋለው ይህንኑ እንዲያደርግ ፈቃድ አለው ብሎ በቅን ልቡና በማመን የሆነ እንደሆነ ውሉ የፀና ይሆናል፡፡
2. ሌላው ተዋዋይ በልጁ አላዋቂነት ያላግባብ የተጠቀመበት ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተፃፈው ድንጋጌ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**<u>አንቀጽ 313 ስለሚመለስ ገንዘብ</u>**

1. አካለ መጠን ላልደሰው ልጅ የተከፈለ ገንዘብ ሊመለስ የሚችለው ውሉ እንዲፈርስ ክስ በቀረበበት ቀን በልጽጐ በተገኘው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡
2. ከዚህ ሁኔታ ውጪ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የተከፈለውን ገንዘብ ለመመለስ አይገደድም፡፡

**<u>አንቀጽ 314 ከውል ውጪ ስለሚደርስ ሀላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ 1 . መሠረቱ</u>**

አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ህገወጥ በሆኑ ሥራዎች ያለአግባብ የበለፀገ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በፍትሐብሔር ህግ ውስጥ ከውል ውጪ የሚደርስ ሃላፊነትንና ያለአግባባ ስለመበልፀግ በተደነገገው መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 315 – 2 አካለ መጠን ሣይደርሱ ደርሻለሁ ማለት</u>**

1. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አካለ መጠን ሣያደርስ ደርሻለሁ ብሎ ቢናገርም እንኳ ይህንን በመናገሩ ብቻ አካለመጠን ባለመድረሱ ምክንያት የሚጠቀምበትን መብቱን አያጣም፡፡
2. እንዲሁም አካለ መጠን ደርሻለሁ በማለቱ ከውል ውጭ የሆነ ሃላፊነትን የሚያመጣ ጥፋት ሆኖ አይቆጠርበትም፡፡

**<u>ንኡስ ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የሞግዚቱ ሕጋዊ ድርጊቶች</u>**

**<u>አንቀጽ 316 በደንብ ስለተፈጸሙ ድርጊቶች</u>**

1. ሞግዚቱ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ የፈጸማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ልጁ አካለመጠን በደረሰ ጊዜ እንደፈጸማቸው ተቆጥረው በኃላፊነት ያስጠይቁታል፡፡
2. ሞግዚቱ በኃላፊነት እጠየቅበታለሁ ሲል ግዴታ የገባበት ወይም በሕግ መሠረት ግዴታ የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ሲል ለፈጸማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ኃላፊ አይሆንም፡፡

**<u>አንቀጽ 317 የሕግ ድንጋጌዎችን ስለመተላለፍ</u>**

የሕግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች ወኪል የሆነው ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሠራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚዎች ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 318 ስለ ሶስተኛ ወገኖች</u>**

1. ፍርድ ቤት ለሞግዚቱ የሰጠውን መመሪያ ሶሶተኛ ወገኖች ካላወቁ ወይም ማወቅ የሚገባቸው ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ መመሪያውን መተላለፉ በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም፡፡

www.abyssinialaw.com

2. አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ ንብረቱን የሰጠ፣ የተናዘዘ ወይም የተወ ማናቸውም ሰው ለሞግዚቱ መመሪያ በሰጠ ጊዜም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 319 ስለ ምትክ ሞግዚት</u>**

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ንዑስ ክፍል ሶስት
## በኃላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች

**<u>አንቀጽ 320 ስለ ሞግዚት</u>**

1. ሞግዚቱ በፈጸመው የንብረት አስተዳደር ጉድለት ምክንያት ወይም መመሪያ ባለማክበሩ ወይም የእርሱ ጥቅም አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ሆኖ እያለ ድርጊቱን በመፈጸሙ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ይጠየቃል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ድንጋጌ በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት
## አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ

**<u>አንቀጽ 321 ችሎታ ማጣት ስለሚቀርባቸው ምክንያቶች</u>**

አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የለውም መባሉ የሚቀረው፡-

ሀ. አካለ መጠን ሲደርስ፣ወይም

ለ. ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ይውጣ ሲባል ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል አንድ
## ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት

**<u>አንቀጽ 322 ጋብቻ</u>**

አካለ መጠን ያልደሰ ልጅ በዚህ ሕግ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ /2/ ሥር በተመለከተው መሠረት ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ በጋብቻው ምክንያት ብቻ ከሞግዚት አስተዳዳር ነፃ ይወጣል፡፡

<u>አንቀጽ 323 በልዩ ሁኔታ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት</u>

1. አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አሥራ አራት አመት ሲሞላው አሣዳሪው ወይም ሞግዚቱ ወይም ያገባኛል የሚል ሌላ ሰው ከሞግዚቱ አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ መጠየቅ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤት ጥያቄው ሲቀርብለት የልጁን ሁኔታና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ የተጠየቀበትን ምክንያት ተመልክቶ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መሆኑ ለልጁ የሚጠቅም ሆኖ ካገኘው ጥያቄውን ተቀብሎ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 324 ውጤቶች</u>**

ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣ ልጅ በሕግ ረገድ አካለመጠን እንደደረሰ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

**<u>አንቀጽ 325 የማይሻር ስለመሆኑ</u>**

1. አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ የተሰጠ ፈቃድ ሊሻር አይችልም፡፡
2. በጋብቻ ምክንያት የተገኘው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የመሆን ሁኔታ ጋብቻው ቢፈርስም እንኳ ውጤቱ እንደተጠበቀ ይቀራል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተደነገገው ቢኖርም ጋብቻው የፈረሰው ለጋብቻ የተፈቀደው ሕጋዊ እድሜ ባለመጠበቁ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ሊወስን ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

የሞግዚትነት ሥራ ሂሣቦችን ስለማስታወቅ

**<u>አንቀጽ 326 መሠረቱ</u>**

1. ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራው ሲያበቃ ሞግዚት ሆኖ ለአስተዳዳሪው ሰው ወይም ለወራሾቹ የአስተዳደረበትን ሂሣብ ማቅረብ አለበት፡፡
2. እንዲሁም በሞግዚትነት ያስትዳደረውን ሰው ንብረት ሁሉ ማስረከብ፣የመብቶቹን ሁኔታና የሚገደድባቸው እዳዎች ካሉም ማስታወቅ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 327 የንብረቶች መዝገብ አለመግባት</u>**

1. ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን በያዘበት ጊዜ ወይም አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ በውርስ ሀብት ሲሰጠው የንብረቶቹን ዝርዝር በመዝገብ ከመያዝ ችላ ያለ እንደሆነ የልጁን ንብረት በውርስ ወይም በስጦት ያገኘውን ሀብት በማናቸውም ሁኔታ ለማስረዳት ይችላል፡፡
2. ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ምስክሮች በሚሰጡት ቃል አንድ ንብረት አካለ መጠን ያልደረሰውልጅ ንብረት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

**<u>አንቀጽ 328 ሂሣቦችን ስለማጽደቅ</u>**

www.abyssinialaw.com

1. ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣው ልጅ የሞግዚቱን ሥራ ሂሣቦች ያፀደቀ እንደሆነና እድሜው ገና አሥራ ስምንት አመት ያልሞላው ከሆነ ሂሣቦቹን ካፀደቀ በኋላ እስከ አንድ አመት ድረስ አጽድቆት የነበረውን ሂሣብ ራሱ ሊያፈርሰው ይችላል፡፡
2. ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣው ልጅ ሂሳቡን እንዲያቀርብ ለሞግዚቱ ፈቃድ ሰጥቶት የነበረ ቢሆንም ከዚህ በላይ ያለው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡
3. አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ አካለመጠን የደረሱ ሲወርሱት እነዚህ ወራሾች የልጁ ሞግዚት ያደረገውን ሂሣብ ያፀደቁት ወይም ሞግዚቱን ሂሣብ ከማቅረብ ነፃ አውጥተውት እንደሆነ ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ጠቅሰው ለመከራከር አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 329 ስለ ይርጋ**

1. አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወኪሎቹ ወይም ወራሾቹ በሞግዚትነት ሥራ ምክንያት በሞግዚቱ ላይ ስለ ኃላፊነት የሚያቀርቧቸው ማናቸውም ክሶች ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን ከተወበት ግዜ ጀምሮ እስከ አምስት አመት ሣያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ በይርጋ ይታገዳሉ፡፡
2. ሆኖም አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረቶቹ እንዲመለሱለት ለመጠየቅ ክስ የማቅረብ መብቱ ከዚህ በላይ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላም ቢሆን አይከለከልም፡፡

**ምዕራፍ አሥራ አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**አንቀጽ 330 ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጐች**

1. የሚከተሉት ድንጋጌዎች በዚህ ሕግ የተተኩ በመሆኑ በክልሉ ውስጥ ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም፡፡

ሀ. በ1952 ዓ/ም የፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ "ስለ ሰዎች" በሚለው መጽሐፍ ከአንቀጽ 198 እስከ 338 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች፣

ለ. በዚሁ የፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ "ስለቤተዘመድና ስለውርስ" በሚለው መጽሀፍ ከአንቀጽ 550 እስከ 825 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች፡፡

2 ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጐች ፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ፣ ውሣኔዎችና የአሠራር ልምዶች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

**አንቀጽ 331 በቀድሞ ሕጎች መሠረት ተገኝተው ስለነበሩ መብቶች**

1. ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ ሕግ በክልሉ ከመጽናቱ በፊት የነበሩ ሕጋዊ ሁኔታዎችን ለማስገኘት አዲሱ ሕግ የሚጠይቃቸው መመዘኛዎች ከድሮው የተለዩ ቢሆኑም እንኳ በቀድሞው ሕግ መሠረት ተገኝተው የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ሁሉ ፀንተው ይቀጥላሉ፡፡
2. ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ ሕግ በክልሉ ከመጽናቱ በፊት በቀድሞው ሕግ መሠረት ተገኝተው የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ያስገኟቸውን ውጤቶች ይህ ሕግ አይለውጣቸውም፡፡

**አንቀጽ 332 ስለምዝገባ**

1. የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳደር ምክር ቤት ይህ ሕግ በሥራ ላይ በዋለ በሁለት አመታት ጊዜ ውስጥ ለሙሉ ተፈጻሚነቱ የሚያስፈልገውን ዝርዝር የምዝገባ ደንብ ያወጣል፤አስፈላጊ ተቋማትንም በክልሉ ውስጥ ያደራጃል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የክብር መዝገብ ሹም ጽህፈት ቤት ተቋቁሞ ሥራውን እስኪጀምር ድረስ በክልሉ ውስጥ አግባብ ባለው አካል የተሰጡ ወይም የሚሰጡ የልደት፣የጋብቻና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ምስክር ወረቀቶች በክብር መዝገብ ሹም ፊት እንደተሰጡ ሰነዶች ተቆጥረው ሕጋዊነት ይኖራቸዋል፡፡

**አንቀጽ 333 በእንጥልጥል ስላሉ የቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች**

1. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በክልሉ ውስጥ በፍርድ ቤት የተያዙ የቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች በተጀመሩባቸው ህግጋት መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡
2. ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በቀድሞው ሕግ መሠረት በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ የተያዙ የፍቺ ክርክሮች በሙሉ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ስልጣን ወዳላቸው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፋሉ፡፡
3. ፍርድ ቤቶቹም እነዚህን ጉዳዮች ተረክበው በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ዉሣኔዎች ይሰጣሉ፡፡

**አንቀጽ 334 ደንብ የማውጣት ስልጣን**

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ ሕግ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችንና መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

www.abyssinialaw.com

**የአማራ ብሔራዊ ክልል የቤተሰብ ሕግ**

**ማውጫ** **ገፅ**

መግቢያ ...................................................... 1

ምዕራፍ አንድ

* ቅድመ ጋብቻ ትጭጭት ...................................................... 4

ምዕራፍ ሁለት

* ስል ጋብቻ አፈጻጸም ...................................................... 6
ክፍል 1 ጠቅላላ...................................................... 6
ክፍል 2 ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ...................................................... 8
ክፍል 3 ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃዎም ...................................................... 11
ክፍል 4 በክብር መዝገብ ሹም ፊት ስለሚፈጸም ጋብቻ ...................................................... 13
ክፍል 5 ሌሎች የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቶች ...................................................... 14
ክፍል 6 ስለ ጋብቻ ምዝገባ ...................................................... 15

ምዕራፍ ሶስት

የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት...................................................... 16

ምዕራፍ አራት

የጋብቻ ውጤት ...................................................... 18
ክፍል 1 ጠቅላላ ...................................................... 18
ክፍል 2 ጋብቻ በተጋቢዎች ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት ......................................................- 21
ክፍል 3 ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ዉጤት ...................................................... 23

ምዕራፍ አምስት

ስለ ጋብቻ መፍረስ ......................................................28
ክፍል 1 በስምምነት ስለመፋታት ...................................................... 29
ክፍል 2 ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍች ......................................................31

ምዕራፍ ስድስት

የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት ......................................................33

ምዕራፍ ሰባት

ጋብቻ ለመፈጸሙ ስለሚቀርብ ማስረጃ ......................................................36

ምዕራፍ ስምንት

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር ......................................................37

ምዕራፍ ዘጠኝ

በጋብቻና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር ረገድ የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን.40
ክፍል 1 ጠቅላላ ......................................................40
ክፍል ሁለት ስለ ፍ/ቤት ሥልጣን ......................................................42
ክፍል 3 ስለ ዕርቅ ......................................................43

ምዕራፍ አስር

ስለ መወለድ
ክፍል 1 አባትነትንና እናትነትን ስለማሳወቅ ...................................................... ...45
ንዑስ ክፍል 1 አጠቃላይ ድንጋጌዎች ......................................................45
ንዑስ ክፍል 2 አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅ ስለመሆኑ ......................................................46
ንዑስ ክፍል 3 ልጅነትን ስለ መቀበል......................................................47
ንዑስ ክፍል 4 በፍ/ቤት ውሣኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ ......................................................51
ክፍል 2 አባትነትን በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የሕግ ግጭት ......................................................53
ክፍል 3 ስለ ልጅነት ማስረጃ ......................................................56
ንዑስ ክፍል 1 በተወላጅነት ላይ ስለሚነሣ ክርክር ......................................................59
ንዑስ ክፍል 2 ስል መካድ ......................................................60

ምዕራፍ አስራ አንድ

ስለ ጉዲፈቻ ......................................................64

ምዕራፍ አስራ ሁለት

ቀለብ የመስጠት ግዴታ ......................................................72

ምዕራፍ አስራ ሶስት

አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች ......................................................78

ክፍል 1 ጠቅላላ ድንጋጌዎች ......................................................78

www.abyssinialaw.com

ክፍል 2 አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ስለሚጠብቁ ተቋማት
...................................................................79
ክፍል 3 የአሳዳሪውና የሞግዚቱ ሥልጣን ..........................................................................................
93
ንዑስ ክፍል 1 አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ .......................................................
93
ንዑስ ክፍል 2 አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር ..................................................
97

ክፍል 4 አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ለመጠበቅ የመለከቱትን
ደንቦች መጣስ ስለሚያስከትለው ውጤት ........................................................................... 107
ንዑስ ክፍል 1 አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሥራዎች .................................................................. 107
ንዑስ ክፍል 2 የሞግዚቱ ሕጋዊ ድርጊቶች .............................................................................. 109
ንዑስ ክፍል 3 በኃላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች...................................................... 110

ክፍል 5 አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ ..................................... .... 111
ንዑስ ክፍል 1 ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት ............................................................ 111
ንዑስ ክፍል 2 የሞግዚትንት ሥራ ሂሣቦችን ስለማስታወቅ ..................................................... 113

ምዕራፍ አስራ አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች.................................................................................................................. 115